# የመስቀሉ ስር ቁማርተኞች


ከዲ/ን

በጋሻው ደሳለኝ

0911-46 41 22


የሽፋን ስዕል
ያሬድ እና ክብሮም


የመጀመሪያ እትም
ታህሳስ 1998
ሁለተኛ እትም
ጥር 1998
ሦስተኛ እትም
የካቲት 1998

## መግቢያ

# መግቢያ የሌለውን ሰው መግቢያ ጻፍ አትበሉት::

# ክፍል 1

## አደጋ ጣዮች

«ከሞአብም አደጋ ጣዮች በየአመቱ ወደ ሀገሩ ይገቡ ነበር» ይላል።
የነገስታቱ መፅሐፍ *2ኛ ነገ 13፥20*

የምንኖርባት ፕላኔት አደገኞች የበዙባት፣ ዋይታና ጩኸት የማያጣት ልዩ የጦርነት ቀጠና ከሆነች ጊዜም እንደ ጅረት እየፈሰሰ አያሌ ዓመታት ተቆጠሩ - - -

ትናንት እንደቀልድ በወንድሙ አናት ላይ የድንጋይ በረዶ ያዘነበው ቃየንና ቃየናውያን የትላንትና ድንጋያቸውን በፕላስተር ቦንብ ለውጠው ዱላቸውን በአዳኝ ጥይት ቀይረው ዛሬ ዓለምን ከዳር ዳር ማንጫጫታቸው ምድር የአደገኞች መኖሪያ፣ የአሸባሪዎችም ዋሻ ብትሆን ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ሆኗል እንዳለው በእርግጥም እንደሆነው ከብዙ ዓመታት በፊት የባህር በር እየሰበሩ አሳቻ ጊዜን እየቆጠሩ ወደ ቅድስቲቱ ከተማ በመግባት አደጋን የሚጥሉና የሠላማዊውን ህዝብ ሀሳም የሚያደፈርሱ ነውጠኞች ግልፅ በሆነ አማርኛ አደጋ ጣዮች ነበር የሚባሉት።

ምሬት፣ ሞትና ጋኔን የተቆራኙት ህሊና ትኩስ ደም እንጅ የሰሊሆም ፀበል ምንም ባይደለበት የእብደት ጠራት ያሻውን ሲገድል ያሻውን ሲያጠፋ እንደጅብዱ ተቆጠረሰት እንጅ ከዚህ ዓለም ውግዘት አልገጠመውም።

የገደለ እንደጀግና የሞተ እንደፈሪ ጠበኛው እንደደፋር ታጋሹ እንደ ሰነፍ በሚቆጠርባት ዓለማችን ሽብርና አሸባሪነት፣ አደጋ ጣዮችና ሞት ባይኖሩ ነበር የሚገርመው።

ምክንያቱም ትናንት ከህሊናዋ ጋር ያልነበረችው ዓለም - «ክርስቶስ ይሰቀል በርባን ይፈታልኝ» ብላ ያልተንጫጫችውን ያህል ዛሬ አንዱ በርባን ሺ አፍርቶ ሺዎቹ በሚሊዮን ተመንዝረው አደጋ ጣዩ በዝቶ እልቂትና ጥፋት መሆኑ ዓለም ስትናንትና በደሏ ዛሬ የምትቀበለው የግፍ ደመወዟ እንጅ ድንገት የተከሰተ የ21ኛው መቶ ክፍለዘመን እንደርቢ አይደለም።

ምንጊዜም ዓለም ከእግዚአብሔር ጥላ ስር ለመውጣት ስታፈገፍግ በአጋጣሚው የሚጠቀሙት የቃየን ልጆች ጦስ ጥንቡሳስ የአሸባሪዎችም መዓበል ሠላሟን ይቀሟታል። እያንዳንዱ የሰከንዶች ሽርፍራፊ ሁሉ በጥይትና በመድፍ ጩኸት መቆራረስ ይጀምራል በአጭር ቋንቋ እግዚአብሔርና መፅሐፍ ቅዱስ ዓለምን ካልመሯት ዓለም በፀጥታ ውስጥ መኖር በፍፁም አትችልም።

ለዚህ ነው መፅሐፍ ቅዱስ «ለክፉዎች ሠላም የላቸውም» የሚለው። *ኢሳ 48÷22*

በሌላ በኩል አደጋጣይነትና ሞት፣ ግደለሽነትና ጥፋት የእግዚአብሔርን አብያተ ክርስቲያናት ያጥለቀለቁበት ዘመን ቢኖር ይህ የምንኖርበትን ክፍለ ዘመን ነው።

አሁን ሰው ሁሉ ከዳን እስከ ቤርሳቤህ ከህፃን እስከ አዋቂ ስለ አፍኒንና ፊንሀስ ስለኤሊም ዝምታና ስለመገናኛው ድንኳን የቸልታ አገልግሎት በሹክሹክታ ያወራል። ሹክሹክታው እውነት ቢሆን እንኳ





ሌዋውያኑን የተናገረ በመብረቅ እንደሚገረፍ እድሜው እንደሚቀጠፍ እየታመነ ፍርሃት፣ ይሉኝታ፣ ባህልና ወግ ግልፅነቱን ቀምተውት ለዘመናት ኖረዋል። ዛሬ ግን ያ ሁሉ ያበቃለት ይመስላል።

የመንጋው ዓይኖች የእረኞቻቸውን ነውር ተመልክተዋል። የደመራው ስር የተቃውሞ ጩኸት፣ የታናናሾችና የታላላቆች ጥላቻ፣ ዋይታና እሪታው ሁሉ በስውር ሳይሆን በግልፅ አንድ ነገር ይናገራል። አደጋ! ከጥላቻ በላይ ምን ዓይነት አደጋ ሊኖር ይችላል?

## አደጋና የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን

ክርስቶስ ባዶ መቃብር እንጅ ባዶ ቤተክርስቲያን አላወረሰንም። አብያተ ክርስቲያኖቻችን ሁሉ በመንጋው ሊሸፈኑ መቅደሶቻችንም በተቀጣጠለ የአምልኮ ስርዓት ሊደምቁ ግድ ነው።

በስሙ ያመኑ ነፍሳት፣ ለርስቱ የተለዩ ካህናት፣ ነገስታትና መኳንንቱ ሁሉ የሰማይን መንግስት በምትወክለው ቤተክርስቲያን ዙሪያ ደጅ ይጠናሉ የማይቋጭ ምስጋና የማይታጉልም ውዳሴ ለስሙ ክብር ይቀጣጠላል።

ደካሞች እንዲበረቱ፣ ህሙማን እንዲፈወሱ፣ በጭንቅና በስቃይ፣ በደስታና በተደላም ያሉ ቢሆኑ የሁሉን ጌታ እርሱን ፍለጋ በቀንና ሌሊት አያርፉም። «ጌታ ሆይ ሁሉ ይፈልጉሃል» *ማር 1÷37*

ይህ እግዘአብሔርን የተራበና የተጠማ ህዝብ ግን አምላኩን በመፈለግ የሚረካው መልካም እረኛ፣ ደግ አስተዳደር ሲኖረውና እራሱን ለእግዚአብሔር መቀደስ በሚችልበት መቅደስ ውስጥ ሲኖር ብቻ ነው።

ሆኑ ተባለ። እናም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በዚህም በዚያኛውም ወገን ይህ ነው የማይባል ሹክቻ ይህ ነወ የማይባል ትርምስ፣ የጉስና የአጥንት ቆጠራ ሃይማኖት፣ እልህ የተቀላቀለበት ስብከት፣ ነቀፋና ትችት፣ ስደትና እስራት የሁልጊዜ እጣ ፈንታ ሆነ። እዚህ ያልተመቸው የቄስ ዘር ወደዚያ ኮበለለ በዚያም ያልተስማማው ያን እየነቀፈ ምህረት እየጠየቀ ወደዚህ ተመለሰ። በመሀል ግን ብዙ ክፍፍል፣ ብዙ ጥፋት ብዙም የመንፈስ ውድመትና ዝለት በሁለቱም ወገን ደረሰ። ትርምሱ ግን ቤተ ክርስቲያንን ጉዳት እንጂ አልጠቀማትም።

በሚያስጨንቅ ሁኔታ እንዲህ የዳመነው አደጋ በኋላ ደፍ ሆኖ ሁሉን ከመጠራረጉ በፊት እንደ ኤልያስ ያሉ ደፋር ነቢያት አክዓብን ሊያስጠንቅቁት የእግዚአብሔርንም መንጋ ዝናቡ ሀያል ነውና 'ወደበረቱ ተሰበሰብ' ሊሉት ግድ ነው።

ዛሬ እንደ ርብቃ መሀፀን ውጥረት የበዛባት ቤተ ክርስቲያን በማህፀኗ በሚተራመሱት ልዩ ልዩ ነፍሳት ምክንያት ዶግማና ትውፊቷ ሰማያዊ ስርዓቷ ሁሉ እንዳልነበር እንዳይሆን ጊዜ ሰጥቶ ማሰቡ፣ ተቀራርቦ መወያየቱ አማራጭ የሌለው መፍትሄ ነው። ችግሩም በሠላም ይፈታ ከተባለ በሁለቱም ወገን የታሪክ አደራን የሚሸከም ለዛሬ ብቻ ሳይሆን ለነገም ጭምር የሚያስብ መንፈሳዊ ሰው ያስፈልጋል ጉዳዩንም የሌሎች እጅ ሳይገባበት በፍቅርና በይቅርታ መንፈስ ወደ መልካም አቅጣጫ ወደ ተሻለ አንድነት መመለስ ግድ ይሆናል እልያ ግን አደጋው ከባድ ነው የ451ዓ. የኬልቄዶን ጉባኤ አስቀያሚ ታሪክ ከብዙ ዘመን በኋላ በዚህ ትውልድ ሊደገም ይችላል።





# ክፍል - 2

## ሐማ ሆይ

*መጽሐፈ አስቴር*

የሐመዳቱ ልጅ አጋጋዊው ሐማ በመርዶክዮስ ምክንያት መላውን አይሁድ ለማጥፋት በንጉሱ ግምጃ ቤት ብዙ ወርቅና ብር መዘነ የሞታቸውንም ጽህፈት አዘጋጅቶ ከህንድ እስከ ኢትዮጵያ ድረስ በመቶ ሃያ ሰባት ሀገሮች በተነው ታላቁ ጽሑፍ ግን በሱሳ ግንብ ላይ ለሁሉ ይነበብ ነበር።

አሁን በፋርስ ማቅ ያልሰበሰ አይሁዳዊ ፤ ዓይኖቹ በእንባ ያልጨቀዩበት የእግዚአብሔር ልጅ ፤ ያላቀረቀረም መፃተኛ አይታይም መቃብር የስነፈጋቸው አፍንጮች፣ ፊት የጣሉ ፊቶች፣ የምድጃ ቁርበት የመሰሉ ግንባሮች፣ የበረገጉ ዓይኖች በፋርስ ሸለቆዎች እንደጨው ተበትነዋል።

ምናልባትም ከጥቂት ቀናት በኋላ በሐመዳቱ ልጅ በሐማ ተንኮል መላው አይሁድ በስደት ሀገር በዚያ ይሞታል መርዶክዮስም በሀምሳ ሜትር ግንድ ላይ በስቅላት ይቀጣል።

ይህ ግን የደካማው ሰው የሐማ ቅዠት እንጅ የእግዚአብሔር እቅድና ሀሳብ አልነበረም። ብዙ ጊዜ ዓለም የራሷን እቅድ በእግዚአብሔር ልጆች ላይ የምታወጣው ከክፋቷ የተነሳ እንጅ በደልና ወንጀል አግኝታባቸው አይደለም።

ለናክሬም በህዝቅያስ ላይ፣ ዳዊት በአርዮን ላይ፣ ጲላጦስም በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ የፃፉት ጽሑፍ እስከአሁን ድረስ መልካም

እንዳልነበረ ይነገራል:: ያም ሆኖ ሐማና ሐማውያን አሁንም በእግዚአብሔር ልጆች ላይ መጸፋቸውን አላቆሙም:: «እስራኤልን የሚጠብቅ ግን አይተኛም ያዕቆብን የሚታደግም አያንቀላፋም» መዝ 120፥4

ይህ ነገር መታደል ከሆነ አስቴር በወገኖቿ ላይ ሞት ታውጆ እርሷ በቤተ መንግስት ኑሮ ጀምራለች::

ጥቂት ሰዎች ስለራሳቸው የተመቻቸ ትንሽ ኑሮ ሲሉ ህሊናቸውን ሸጠው ሞራላቸውን ቀብረው በማያስደስተውና በማይማርከው ስፍራ ለረጅም ዘመን ይኖራሉ:: እነኚህ ሰዎች ለህሊናቸውና ለእግዚአብሔር መኖር ስላቆሙ እጅግ ብዙ የሚያበሳጩ ባህርያትን ተሸክመው ሲንቀሳቀሱ የሁሉ አይን ያያል:: በማያስቀብት ቦታ ሲስቁ በማያሳዝነው ስፍራ ከንፈራቸውን ሲመጡ፣ ሳይገባቸው እናታቸውን ሲነቀንቁ የምናያቸው ሁሉ ፈዘኞችና ከተደረደረላቸው የቂጣ ሰገነት መውረድ የማይፈልጉ ጉደኞች ናቸው::

> ወዳጄ ሆይ ክርስቲያን ከሆንክ ለሆድህ ሳይሆን ለህሊናህ ብቻ ኑር ለህሊና መኖር ከዓለም አሰራር ነፃ መውጣት ነው:: ዲያቢሎስንም መርገጥ ነው::

ነገን የሚፈሩ፣ እውነተኛው ማንነታቸው የከዳቸው ሰዎች እነእርሱ በውስጥ ካለ ከአጥር ውጭ ስላለው ፍጥረት እምብዛም ደንታ ላይኖራቸው ይችላል የአስቴራዊነት ውበቱ ግን ስለ ርካሽ ጥቅማጥቅም ራስን መለወጥ አልያም ድርጎ ባለበት ስፍራ ፋርሽካ እንደጠገበ አሳማ ማንኳረፍ ሳይሆን በደጅ ስላለውና ሞት ስለተፈረደበት ህዝብ ጨክኖ መቆም ነው::





በሐማ ክፉት ሞት የተፈረደባቸው መርዶክዮስና መርዶክዮሳውያን አትርፈን ሲሉ ወደ አስቴር መልዕክት ላኩ:: አስቴር ግን ወደ ንጉስ አርጤክስ መግባት እንደማትችል ህዝቧንም ለማዳን ብዙም እንዳልጓጓች ለመርዶክዮስ ገለጠች::

ተስፋ ሲጨልም ወዳጅ ሲከዳ መሬት የተንሸራተተ ያህል ሰማይ የተደፋም እስኪመስል ይጨንቃልና የተወጠረ ህሊና ሞት ያበሳጨው አንደበት ቀጣን ተመልቶ እንዲህ አለ:: «አስቴር ሆይ ምናልባት አንቺ በቤተ መንግስት ስለሆንሽ በአይሁድ ሁሉ ላይ ከታወጀው ሞት እድናለሁ ብለሽ አስበሽ ይሆናል ነገር ግን ለዚህ ህዝብ መዳን ከሌላ ስፍራ በሆነለት ጊዜ አንችና የአባትሽ ቤቶች ሁሉ ታፍራላችሁ» በእርግጥም ጠንካራ ቃል ነበር::

አሁንም እንደ አስቴር በህዝባቸው ላይ ሞት ታውጆ እነእርሱ ግን በተመቻቸው ስፍራ የሚኖሩ እንደ ጴጥሮስ የጌታቸው ገላ ጅራፍ ሲያስተናግድ እነእርሱ ብርድ መቋቋም አቅቷቸው ከፖለቲከኞች ጋር እሳት የሚሞቁ እንዲህ ዓይነቱን የመጽሐፍ ቅዱስ ግልፅ ቃል ሲሰሙትና ሲያደምጡት ግድ ነው::

ለዘመናት በየገዳማቱና በጌርጌሴኖን ሥፍራ አስርና ሶስት አስርት አመታት የሃይማኖት ትምህርት ደክመው ተምረው ዛሬ ግን በዋንዛ እንጨት የተሰራ ሙዳየ ምጽዋት አንገታቸው ላይ ታስሮላቸው ደጅ የሚጠኑ ወደ ቤተመቅደሱ ገብተው የማገልገል እድል የተነፈጋቸው ሁሉ ሞት የታወጀባቸው የዚህ ዘመን መርዶክዮሶች ናቸው::

ጌታ አምላክ የለበሱትን የሀዘን ማቅ በልዩ ጥበብ ይለውጥልን የአይሁዳዊው የመርዶክዮስ ቃል በአስቴር አጥንት ውስጥ እንደ ቀባት በቀለጠ ጊዜ አስቴር ሳትወድ በግዷ በንጉሱ ፊት ለመቆም እራሷን

አዘጋጀች። በንጉስ አርጤክስም ፊት ሞገስ ባገኘች ሰዓት ንጉሱንና ሐማን ወደመጀመሪያው የወይን ጠጅ ግብዣ ጠራቻቸው። ይህም ሆነ።

በዚህ ቀን ግን አስቴር ከንጉሱ የምትፈልገውን ነገር አልጠየቀችም ንጉሱ የምትሰምነውን ለማወቅ ቢጓጓ እንኳ ሌላ ተጨማሪ ቀን አስፈለጋት።

ማንኛውም ክርስቲያን ስኬት ያለውና አስተማማኝ ስራዎችን እንዲሰራ ከተፈለገ ከእግዚአብሔር ተጨማሪ የዝግጅት ጊዜዎችን መጠየቅ አለበት ምክንያቱም እግዚአብሔር ስልጆቹ ከዛሬ ይልቅ ነገ የተሻለ ይሰራልና ነው።

በዛሬና በነገ መካከል ግን ጠንከር ያለ ጨለማ የማይጋፋት ሌሊት እንዳለ አትዘንጋ። ውርጭ የቋጠረው ነፋስ፣ ዝምታና ድንጋጤን ያዘለው ውድቅት፣ የማይገፈፈው ጨለማ ሁሉ የሌሊቱ ክፍል አንዱ ገጽታ ነው።

ጨለማውን የምትታገስበት መልካም የእንቅልፍ ሠረገላ ካለህ ሌሊቱን ትወጣዋለህ እንቅልፍህ ግን በፍራሾችህ ላይ ሳይሆን በአምላክህ እቅፍ ላይ ይሁን። እርሱ የታቀፋቸው በፍፁም አይወድቁምና።

ሆኖም እግዚአብሔር ብቻ የሚሰራባቸው ለእርሱ የተለዩ ሌሊቶች እንዳሉ አትዘንጋ በእነዚያ የጌታ ሌሊቶች የሚሰሩ ስራዎች ሁሉ ተመልካቹን በአግራሞት እጁን አፉ ላይ የሚያስጭኑ ናቸው።

በእግዚአብሔር ሌሊት ንጉስ አርጤክስ እንቅልፍ አልወሰደውም ይህ ሌሊት እግዚአብሔር ስመርዶክዮስ የሚሰራበት





ሌሊት ነበር አንተም ማቅ ለብሰህ በንጉሡ በኢየሱስ በር ላይ በእምነት ብትቀመጥ ጌታ ይሰራልሀል።

ንጉሱ በአንድ ወቅት ገበታና ታራ የተባሉ ሁለት ሰዎች በእርሱ ላይ መፈንቀለ መንግስት አስበው ሲመክሩ ደርሶ መርዶክዮስ አድኖታል። ይህ ቁም ነገርና ይህ ታሪክ ከሰዎች ልቦና ቢጠፋ እንኳ ጥቅልሉ መፅሐፍ ግን ለዘመናት ሲያስታውሰው ይኖራል።

ወዳጄ ሆይ አንተም ሰዎች ሳይሆኑ መፅሐፍ የማይረሳውን መልካም ስራ ሰርተህ እሰፍ አንድ ቀን ትነሳባታለህ።

ንጉሱ የተፃፈውን ታሪክ አንብቦ ሲጨርስ መርዶክዮስ የት እንዳለና ንጉሱን በማዳኑ ምክንያት ምን እንደተደረገለት ጠየቀ።

ይህ ጥያቄ ለዛሬዋ ቤተ ክርስቲያን ቢቀርብላት መልሷ ምን ይሆናል ብለህ ትገምታለህ?

ለቤተ ክርስቲያን ውለታ የዋሉላት፣ እንደጧፍ የነደዱላትና በእውነት የቆሙላት ሁሉ አሁን በልዩ ልዩ ምክንያት ከቅፅሩ ውጭ ነው ያሉት። ሐማና ሐማውያንን ግን ምናልባት በውስጥ የጮማ ቢለዋ ይዘው ሲንጐራደዱ ታያቸው ይሆናል። ሐማ ለኔ የጠገበ አሳማ ነው ሆድ እንጂ ህሊና የለውም።

ንጉስ አርጤክስ ለመርዶክዮስ ምንም እንዳልተደረገለት ባወቀ ጊዜ ሐማን ጠርቶ ለመርዶክዮስ የወርቅ ካባ እንዲደረብለት፣ ዘውድም እንዲያቀዳጁት፣ በበቅሎ ላይ እንዲቀመጥና ሐማም ልጓሙን ይዞ ፈረሱን እየጎተተ ከተማውን እንዲያዞረው ህዝቡም ለእርሱ እንዲሰግዱ አዘዘ። ይህ ነው እንግዲህ የመጠበቅ ውጤት።

ዛሬ በብዙ ነገር የጌታን እርዳታ የሚሹ ሰዎች መጠበቅን እንደ ጊዜ ማጥፋት እየቆጠሩት ወደ ስጋ አማራጮቻቸው በመሄድ ላይ ናቸው እውነቱ ግን እርሱን በመጠበቅ የሚጠፋ ጊዜ፣ የሚባክንም ሰዓት አለመኖሩ ነው:: ክርስቲያኖች በሃይማኖት ሆነው እግዚአብሔርን ሲጠብቁ ሰዓታቸውን በአግባቡ እየተጠቀሙበት እንጅ እያባከኑት እንዳልሆነ ዓለም መረዳት አለበት:: በተለይ እግዚአብሔር በክርስቲያኖች ላይ ያለው የመጨረሻዎቹ ሰዓቶች እጅግ ጣፋጭ ሆነው በእርሱ የተቀመሩ ናቸው::

ሐማ መርዶክዮስ የተቀመጠበትን በቅሎ ሲጐትት ውሎ ወደ ቤቱ ሲገባ ሚስቱና ቤተሰቡ እንዲህ እያሉ ተቀበሉት «ሐማ ሆይ በፊቱ መዋረድ የጀመርክለት መርዶክዮስ ሳያጠፋህ አይተውህም»

በእርግጥ ቁማርተኛው ሐማ ከመርዶክዮስ አምላክ ጋር ታግሎ ማሸነፍ አይችልም መቃብር ያስቆፈረለትን ሰው ዛሬ በቅሎ ላይ አስቀምጦ ሲያንሸራሽረው መዋሉ ለነገ ውድቀቱ የማረጋገጫ ፉጨት ነው::





# ክፍል - 3

## የመስቀሉ ብድራት

የስልጣኔአችን ጥንት፣ የእውቀታችንም ጥግ፣ ፍርሃትና ድፍረታችን የእምነታችን ሁሉ መሠረት ጌታ አምላክ እግዚአብሔር ነው::

እግዚአብሔር ስንል ደግሞ አብን ወልድን መንፈስ ቅዱስን ማለታችን እንደሆነ የእግዚአብሔር ልጆች ልብ ይሏል::

የዘመኑም ፍፃሜ በደረሰ ጊዜ ከሦስቱ አካላት አንዱ እግዚአብሔር ወልድ (ኢየሱስ ክርስቶስ) በስጋ ተገልጦ በተመሳቀለው ቅዱስ እንጨት ተሰቅሎ አድኖናል::

ውዳሴና አምልኮ ከምድር እስከ አርያም ድረስ ለገናናው ስሙ ይሁን:: አሜን::

ምናልባት አሁን ሁላችንም ዓይኖቻችንን ስንከፍት ዓለም በማያስገርም ትርምስ አልያም በማያስፈራ ጨለማ ተሞልታ ሲሆን ይችላል:: ሆኖም የዓለም ግርዶሽ የዜጐቿን ማንቀላፋት እንጅ የክርስቶስን መስቀል መወገድ ፈጽሞ ስለማያሳይ መሻቱ ካለ ድቅድቅ ጨለማውንም ቢሆን አቋርጦ የጌታን መስቀል መመልከት ይቻላል:: «ለሚያምን ሁሉ ይቻላል» እንዲል *ማር 9፥23*

ከብዙ ዓመታት በፊት በእንጨት ተሰቅሎ የሞተ ሁሉ «የተረገመ ነው» የሚል የአዋጅ ቃል ለሁሉ ይነበብ ነበር:: *ዘዳ 21 ፥23*

ጌታ አምላክ እግዚአብሔር ግን ከህግ እርግማን ሊዋጀን በወደደ ጊዜ ዘመንን ለሁለት በከፈለበት በአንድ ልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከሞት እዳ ነፃ አውጥቶናል::

በብሉይ ኪዳን መፅሐፍ እንደሚተርከው በደል ወይም ኃጢአት የተገኘበት ሰው ለኃጢአቱ ማስተሰሪያ የሚሆን በግ አልያም ፍየል አምጥቶ ሊቀ ካህኑ እየረዳው፣ እጁን በበጉ እናት ላይ ጭኖ በሀጢአቱ ይናዘዝ ነበር:: ካህኑም ያንተ ሀጢአት ወደዚህ በግ ይለፍ በአንተ ፈንታም ይህ በግ በደለኛ ይሁን እያለ ይመርቀው ነበር:: በመጨረሻም ከዚህ አስገራሚ ሰሎት በኋላ በጉ ከከተማ ውጭ ይወሰድና ስለሰውየው ቤዛ ሆኖ በመሰዊያው ላይ ይሰዋል::

«ስለዚህ ኢየሱስ ደግሞ በገዛ ደሙ ህዝቡን እንዲቀድስ ከበር ውጭ መከራን ተቀበለ» *ዕብ 13÷12*

ከጥንታዊው ሰው ጀምሮ እስከ በርባን ድረስ፣ ከቃየን ልጆች አንስቶ በቀኙ እስከተሰቀለው ወንበዴ ሁሉም እጁን በእርሱ ላይ አኖረ እርሱም መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ የሰዎችን ሁሉ ኃጢአት ተሸክሞ ወደ መስቀሉ ጫፍ በፍቅር ወጣ ያን ጊዜ በሁላችንም ህሊና የማይጠፋና የማይደበዝዝ እውነት ለዘለዓለም ታተመ::

እነዚህ ጥቅሶች በሙሉ የመስቀሉ ፍቅር በነካን ወራት ከቅዱሱ መጽሐፍ አንብበን የተናገርናቸው ግሩም ጥቅሶች ናቸው::

«እርሱ ግን ስለመተላለፋችን ቆሰለ ስለበደላችንም ደቀቀ የደህንነታችንም ተግሳፅ በእርሱ ላይ ነበረ በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን - - - እግዚአብሔርም የሁላችንንም በደል በእርሱ ላይ አኖረ::» *ኢሳ 53÷5*





«በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ህይወት እንዲኖረው እንጅ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶታልና» *ዮሐ 3÷16*

«ነፍሱን ስለወዳጆቹ ከማኖር ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም» *ዮሐ 15÷12*

«ጠላቶቹ ሳለን ከእግዚአብሔር ጋር በልጁ ሞት ታረቀን» *ሮሜ 5÷10*

አሁን ዓለም ያሻውን ይበል እንጅ ይህ የእስከ ዘለዓለም እውነት በእግዚአብሔር ልጆች ልቦና ለምን ጊዜውም ታትሟል:: ከቀራንዮ ጫፍ በዓለም ላይ የሚንቦገቦገው የመስቀሉ ብድራት በእርሱ ለሚያምን ሁሉ የሁል ጊዜ ኩራት ነው::

ዓለም የክርስቶስን መስቀል የምትቀብርበት የቆሻሻ ጉድጓድ እንጅ የእግዚአብሔርን ፍቅር የምታይበት ብሩህ ዓይኖች የላትም:: እስከ አሁን ድረስ ለእርሷ ክርስቶስ ወንበዴ በርባን ደግሞ ንፁህ ሰው ነው:: ስለዚህ ዓለም አመለካከቷን የምታጠራበት የእውነት ኩል ያስፈልጋታል::

የሚገርመው ነገር ግን ዓለም እንደምታስበው የጌታ መስቀል መቃብር እርሷ ያዘጋጀቻቸው የቆሻሻ ጉድጓዶች ሳይሆኑ የክርስቲያኖች ልብ መሆናቸው ነው:: በልባችን የተቀበረውን የመስቀል ፍቅር በየትኛውም መንገድ ለማውጣት መሞከር ትርፉ ድካም ነው::

ቅዱስ ጳውሎስ ስለ መስቀል ጠላቶች እንዲህ ብሎ እንደጻፈ እናውቃለን «ብዙዎች ለክርስቶስ መስቀል ጠላቶች ሆነው ይመላለሳሉና ብዙ ጊዜ ስለ እነርሱ እላችኋለው አሁንም እንኳ እያለቀስኩ እላለሁ:: መጨረሻቸው ጥፋት ነው ሆዳቸው አምላካቸው

ነው ክብራቸው በነውራቸው ነው ሀሳባቸው ምድራዊ ነው እኛ ግን ሀገራችን በሰማይ ነው ከዚያም ደግሞ የሚመጣ መድኃኒትን እርሱንም ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን እንጠባበቃለን።» *ፊሊጲ 3፥ 18*

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል እንጨትም ይሁን ብረት ድንጋይም ይሁን ፕላስቲክ ለምናምንበት ለኛ ሕይወት እንጅ ሞት አይደለም «የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት ነው ለኛ ለምድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነው» *1ኛ ቆሮ 1፥18*

ጥቂት ወገኖች ግን እንደ ስህተት ሽንገላ ባለ የዓለም ትምህርት እየተወሰዱ በጌታ መስቀል ላይ ልዩ ልዩ ነገር ይናገራሉ ። ለእነዚህ ወገኖች የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር የመስቀሉን ብድራት እንዲመለከቱ አይኖቻቸውን ያብራልን ከማለት ውጭ ለሰው ልጆች የማሆን የከረረ እርግማን የለንም። «የሚያሳድዷችሁን መርቁ እንጅ አትርገሙ» *ሮሜ 12፥14*

የጌታ መስቀል ግን የማይለወጥ የእስከ ዘለዓለም እውነት ነው። ምን ጊዜም መስቀሉን ስናስብ ባህረ እሳትን እንደምንሻገር ተስፋ እናደርጋለን። ወደ መስቀሉ ስንመለከት ደግሞ የነቢያቱን ትንቢት፣ የጠቢባኑን ምሳሌ፣ የአዛውንቱን ተስፋ፣ የሀያላኑን ጅግንነት፣ የሊቃውንቱን ትምህርት፣ የጌታን ምህረት፣ የጠላትን ሽንፈት፣ የነፍሳትን ደስታ፣ የሰማዕታትን ፅናት፣ የመሳፍንቱን ጉልበት ሁሉ በእግዚአብሔር ልጅ መዳፍ ተከማችቶ እናገኘዋለን።

ያለ ኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ክርስትናን ማስታወስ አይቻልም። እኛ አምላካችንን የምናውቀው ከነመስቀሉ ነው።





# ክፍል - 4

## የነቀዙ አጥንቶች

ክርስቶስ ኢየሱስን ወደ መስቀሉ ጫፍ ገፍተው ካወጡት ሰዎች መካከል ቀደምቶቹ የምቀኝነት መንፈስ ሰለባዎች ናቸው።

ማንም ሰው ምቀኝነት የትና እንዴት እንደሚጀመር በእርግጠኛነት አያውቅም። ብቻ አንድ ሰው የመበስጥ ስሜት ሲሰማውና በራስ የመተማመን መንፈሱ ሲከዳው ሳያስበው እራሱን ምቀኛ ሆኖ ያገኘዋል።

ምቀኝነት መልካም የሆነውን ያለመውደድ ጉስቋልናና የበጉ ህሊና ድህነት ነው። ብዙ ሰዎች ምቀኝነትን እየተፀየፉ ሳያውቁት ለብሰውት ይዞራሉ። ወዳጄ ሆይ አንተ ግን መጥላት ካለብህ ምቀኝነትን ከልብህ ጥላ ክቅናት ፊትም የጦር ውርወራ ያህል ራቅ። እኒህ አጥንትን የሚያነቅዙ ባክቴሪያዎች ናቸውና።

### «<u>ቅንዓት አጥንትን ያነቅዛል</u>»

ጥቂት ሰዎች ለእንዲህ አይነቱ አስቀያሚ ተግባር ተላልፈው የሚሰጡት ህይወት ለዋጩን የክርስትና ትምህርት ወደ ልባቸው ማስገባት ሲሳናቸው ነው። በክርስትና ትምህርት ውስጥ ቅናትና ምቀኝነት ያሽማቅቃሉ እንጅ አያኮሩም።

ለዚህ መልካም ምሳሌ የሚሆነን የኢየሱስ ክርስቶስ ድንቅ ትምህርት ነው። እንድ የወይን አትክልት ጌታ ለእርሻው ሰራተኞችን መቅጠር ፈልጎ ማልዶ ተነሳ ይላል ታላቁ መጽሐፍ። ከዚህ በኋላ በቀን ውሎ አንድ አንድ ዲናር ሊሰጣቸው ተስማምተው ስራ ጀመሩ።

ሰራተኞቹ ስራ የጀመሩበት ሰዓት ግን ይለያይ ነበር ከመካከላቸው ከጠዋቱ ሦስት ሰዓት የጀመረ አለ፣ ከቀኑም በስድስት ሰዓት የተቀጠረ አለ፣ በዘጠኝና በአስራ አንድ ሰዓትም የተቀጠሩ ነበሩ በመጨረሻ ግን ስራቸውን ጨርሰው ወደ ቤታቸው ለመሔድ ሲነሱ የወይኑ አትክልት ጌታ ለሁሉም ሰራተኞች እኩል አንድ አንድ ዲናር ከፈላቸው።

ይሄኔ ቀደም ብለው ማለዳና ረፋድ ላይ የተቀጠሩት ሰራተኞች በወይኑ አትክልት ጌታ ላይ አጉረመረሙ «እንዴት ዘግይተው የተቀጠሩትን ሰዎች ከኛ እኩል ይከፍላችዋል» ብለውም ተንጨረጨሩ የወይኑ ጌታ ግን በትዕግስት እንዲህ አላቸው።

«ወዳጆቼ ሆይ እኔ ማናችሁንም አልበደልኩም ቀኑን ሙሉ በአንድ አንድ ዲናር ልትሰሩ ተስማምተን አልነበረምን? ያላችሁኝን ከፍያችኋለሁ። ረፋድ ላይ ለተቀጠሩት ሰራተኞች ግን ከእናንተ እኩል አንድ አንድ ዲናር መክፈሌ እናንተን አይጐዳም ከጐዳም እኔን ነው የሚጐዳው። ደግሞስ በገዛ ገንዘቤ የወደድኩትን ላደርግ መብት የለኝምን? ወይስ እኔ መልካም ስለሆንኩ የእናንተ አይኖች ምቀኛ ናትን?» ሲል ተናገራቸው። ***ማቴ 20፥1-16***

በእርግጥ እንደ ጌታ ቃል ምቀኛ በቅናት ማየት ሲጀምር ከአይኖቹ የእሳት መዓበል ይፈሳል ቁጣውም እንደ ክፉት ስራዊት ነው።

## «<u>በቅናት ፊት ማን ይቆማል</u>»

ምቀኛ የገዛ ሰውነቱ ሌሎችን የሚጠቅም መስሎ ከታየው ልብሱን አውልቆ ጉንዳን ላይ ይቀመጣል።





ምቀኛ ካልተቅበዘበዘ እንደ ታመመ አትጠራጠር። መቅበዝበዝ ያቆመ ምቀኛ ወይ ታሞ ነው አልያም ሰግሞ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ «እግዚአብሔር መልካም ነው በመከራም ቀን መሸሸጊያ ነው» ይላል ት. ናሆ 7፥1 መልካሙ እግዚአብሔርን አለመውደድና ልጁንም አይቶ ከመሬት ተነስቶ መጥላት ፍጥጥ ያለ ምቀኝነት እንጅ ምንም አይነት አንድምታ የለውም። «ባየነውም ጊዜ እንወደው ዘንድ ደም ግባት የለውም። የተናቀ ከሰውም የተጠላ የህማም ሰው ደዌንም የሚያውቅ ነው - - » ***ኢሳ 53፥2***

የአይሁድ ረበናት በአሸንክታባቸው ሲያጃጅሉት የነበረውን ምስኪን ህዝብ የእግዚአብሔር ልጅ በፍቅር ማርከባቸዋልና ተቆጡ። ቁጣ ቅናትን፣ ቅናት ምቀኝነትን፣ ምቀኝነት አጋጣሚዎችን አመቻችቷልና ንፁህን በግ ኢየሱስ ክርስቶስን ለሞት አጣደፉት - -

ምቀኝነት ካንሰር ነው። በጌታ ዘመን የነበሩት ሰዎች ይልቁንም /ካህናቱ/ እጅጉን የቆጫቸው ጌታ ከእነርሱ ጋር ሳይሆን ከቀራጮችና ከአመንዝሮች ይልቁንም በዓለም ከተዋረዱት ጋር መዋሉ ነው። በእርግጥ ሊቀ ካህናት እንደመሆኑ ያለመጠን ተኮፍሶና ተሽፋፍኖ በምኩራብ አካባቢ መሰንበት ነበረበት? አይመስለኝም።

ጌታዬን አውቀዋለው ቀሚስ በመቀያየር ጊዜ የማያጠፋ፣ መቀመጥ ሳይሆን ማገልገልን የሚናፍቅ፣ ታናናሾችን ማይፀየፍ ለደሃ አደጉ የሚያነባ በብዙ ነገር የተፈተነ ሊቀካህን ነው።

ይህ ህይወቱ ለብዙዎች ተምሳሌት ለጥቂቶች ደግሞ ቅናት ቀስቃሽ ትክሳት ነው። ይሁን እንጅ በጌታችን ላይ የሚቀና ቢኖር እንደ ተበሳጨ ክፉ ውሻ የገዛ ሰውነቱን ነክሶ ይገላል እንጅ

አንዱ የእግዚአብሔር ልጅ በሁሉ ፊት እንደበረደ በነፃም በጲላጦስ አደባባይ ግን በሉሲፈርና ልጆቹ የቀረበበት ክስ ይሰለኝ ነበር::

- ❖ ራሱን የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ይላል *ሉቃ 22÷70*
- ❖ አባቶቻችን 40 ዘመን ሙሉ የገነቡትን መቅደስ አፈርሰዋለው እያለ ይዝታል::
- ❖ ለቄሳር ግብር እንዳንገብርለት ይከለክለናል
- ❖ እሉተ ሰንበትን ይሽራል የሚሉትና የመሳሰሉት ዋናዋናዎቹ ናቸው::

የሀሊና ዳኝነት በጠፋበት በዚያ ወራት፣ ከሰማርያ እስከ ይሁዳ ከገሊላ እስከ ጲላጦስ አደባባይ የተሰለፈው ሁሉ በሮማውያኑ ችሎት ፊት «ስቀለው ስቀለው» ብሎ መጮሁ እኒህን የሀሰት ክሶች እያስተጋባ እንጅ እውነት በደል አግኝቶበት አይደለም::

በጥብርያዶስ ወንዝ ዳር አሳ የበላም፣ በሰሊሆምና በቤተ ሳይዳ የተፈወሰም፣ አብሮት ያደረው የዋለው ሁሉ ዛሬ ቀን ከፍቷልና እየጮኸና እያስተጋባ አንድ መዝሙር ብቻ ይዘምራል «ይሰቀል - - - ይሰቀል - - - ይሰቀል» የሚል

ለእውነት ስትቆም፣ ለህሊናህ ስትታመን ዓለም በአንተ ላይ መዝገብ ሙሉ ክስ አለት:: ዓላማዋም አንተን መወንጀልና በጉስቁልና መቅሰፍት መምታት ብቻ ይሆናል::

ያጨበጨበልህ ህዝብ ሲያጨበጭብብህ፣የመረቀህም ሲረግምህ ያደነቀህ ሰው ሲነቅፍህ ጊዜው እየቀረበ እንደሆነ አስተውል እንጂ እምብዛም





አትጨነቅ:: ንፅህናህ ሳይጠፋት መልካምነትህ ሳይሰወራት በከንቱ ለምታጉላላህ ዓለም ንፁህ ሰው ነኝ ብለህ መልስ ለመስጠት አትዘጋጅ:: እውነትን ብትመልስላት እንኳ የእርሷ ልብ ያለው ካንተ መልስ ጋር ሳይሆን ወደ ፊት ከምታቅድልህ ዕኑ መከራ ጋር ነው::

በቅዱሱ ላይ ያለህ እምነት እንደ አድማስ ዓለት የጠነከረ ከሆነ ግን ነገን ተሻግረህ በድል ትንዛለህ::

ጽድቅን እንደምናደርገውና ትሩፋትን እንደምንሰራው ሁሉ በአንፃሩ ለክርስቲያን የማይመቸውን ርኩሰት እየፈጸምን ክርስትና እየመሠለን የከሳሽነት መንፈስ ጊዜያችንን የቀማብን ብዙዎች ነን::

ከሳሾችን በኮነንበት ማግስት መዝገብ ይዘን መቆማችን ተጨቃጫቂዎችን በተፀየፍንበት ለሞን የሰየልን አለባልተኞች መሆናችን ክርስትናችንን ጥያቄ ውስጥ ጣለው እንጅ ብዑዓን አላሰኘንም:: ጥቂት ክርስቲያኖች ለእግዚአብሔርና ለቤተክርስቲያን የቀናን በሚመስልበት ወራት የገዛ ወንድሞቻችንን ስናሳድድ እህቶቻችንንም ስናሰቃይ መቆየታችን ከትዝብት ጣለን እንጅ ዘውድ ኒሻን አላሸለመንም::

ያልበረታና ያልጠነከረ ክርስቲያን ከመማሩና እራሱን በጽድቅ ጌጥ ከማስዋቡ በፊት ስለእግዚአብሔር ቢቀናና ስለ ቤተ መቅደሱም ጥብቅና ቢቆም ደስታው ስፍር ቁጥር የለውም:: ለዚህ ይመስላል ጥቂት አዳዲስ አማኞች በአንድ ጀምበር መንግስተ ሰማያት ተገብቶ ይታደር ይመስል ሁሉ ዛሬ ካልቀና ሁሉ ዛሬ ካልተስተካከለ ደስ የማይላቸው:: እነዚህ ከጌታ ፈቃድ ይልቅ የዓለምን መንገድ

በፊት ህሊና በራሱ እውነት በመሆኑ ነው:: ማንኛውም ሰው ከመዋሸቱ በፊት እራሱን ይዋሻል እውነትም ሲናገር ቀድሞ ለራሱ ይናገራል:: እጅና እግሩን ህሊናው ውስጥ ቀብሮ የማይኖር ሰው ከሚሳሳተው የሚስተው ይበረክታል:: ከትላንትና ስህተቱ ለዛሬና ለነገ የሚቆጥብ ሰው የዚህ ዓለም ጉስቋላ ነው:: ህሊና የማያታልሉትና የማይታለሉበት እውነት ነው::

ወደ ቀደመው ነገራችን እንመለስ ሮማዊው ፈራጅ ጲላጦስ እውነት ምንድን ነው? ብሎ መጠየቁ ፖለቲካን እንጅ እውነትን አጥርቶ ባለማወቁ ነው:: እውነትን የኢየሱስ ክርስቶስ ከሳሾች አይሁድም፣ ዳኛቸው ጲላጦስም አያውቋትም እውነት ለሆዳቸው ሳይሆን ለህሊናቸው በታመኑ ሰዎች መዳፍ ናት::

በሌላ በኩል ግን መካሰስና መወነጃጀልን በጲላጦስ አደባባይ ብቻ ሳይሆን በተቀደሰውም ስፍራ በመቅደሱ ውስጥ እንኳ እንደ ቀልድ ልታይ ትችላለህ:: በአምላካችን አደባባይ ሲጮሁና ሲያለቅሱ፣ ሲወድቁና ሲነሱ እንዳበደ ሰው ሲወናጨፉ የምታያቸው ሰዎች ሁሉ እውነትን የተቀሙና የተዘረፉ ናቸው:: በዓለም ባለው ፍርድ ቤት ዶሴ ይዘው የተሰለፉትም የእውነት ያለህ የሚሉ ናቸው::

በእርግጥ እውነትን በህግ ማፈላለግ ሀጢአት ነው ባይባልም እውነትን የማያውቁ ዳኞች በተጉለቱባት የአለም ፍርድ ቤት መነታረኩ ምሬት ያደርቅ እንደሆነ እንጅ ጠብ የሚል ነገር አይኖርም:: እውነተኛው ፈራጅ እግዚአብሔር ብቻ ነው::

መጽሐፍ ቅዱስ «ከእናንተ አንዱ ከባልንጀራው ጋር ሙግት ቢኖረው በቅዱሳን ፊት በመፋረድ ፋንታ በዓመፀኞች ፊት ሊፋረድ





ይደፍራልን? ቅዱሳን በዓለም እንደሚፈርዱ አታውቁምን?» ይላል *1ኛ ቆሮ 6፥1*

እውነትን የሚናገሩ ቅዱሳን ከመቅደስ ሲጠፉ፣ ለእውነት የቆመን የጻድቅ ዘር አረምና ዋግ ሲመታው በውስጥ የተበደሉ ጥቂት አማኞች ከጥቂት እውነት ጋር ወደ ዓለም ፈራጆች ይገሰግሳሉ አንድ የሚገርም እውነት ቢኖር ግን በዚያ የሚያገኙት እውነተኛውን ፈራጅ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ሳይሆን ስለ እውነት ግራ የተጋባውን ጲላጦስንና ጲላጦሳውያንን ብቻ ነው:: እውነት ግራ ያጋባችው ጲላጦስ ደግሞ የፈሰገው ቢሆን እውነተኞቹን የእግዚያብሔርን ልጆች ሳያስገርፍና ሳያስቅላቸው አይቀርም::

## ***<u>ማን ያገልግል</u>***?

ኢየሱስን እያገለገሉ ከገሊላ የተከተሉት ብዙ ሴቶች በሩቅ ሆነው ሲመለከቱ በዚያ ነበሩ:: ማቴ. 27 ፥ 55

አገልግሎት የአገልጋይ ህይወቱ ነው:: ጌታውን እንዴት ማገልገል እንደሚገባው የማያውቅ አገልጋይ ካርታ ያልያዘን መርከበኛ ይመስላል መቅዘፋን እንጅ ወዴት እየተጓዘ እንዳለ እንኳ በውል አያውቀውም::

የመነቸከ ስብከት፣ የደነዘዘ እልልታ፣ የማያሳርፍ ጸሎት ልብ የማይነካ ምስጋና ሁሉ ለእግዚአብሔር ያልተሰጡ አገልጋዮች በሚርመሰመሱበት ተራራ ላይ ነው :: ወደ ተራራው ማን እንደወሰዳቸውና ለምን ዓላማም በዚያ እንደቆሙ በውል ያልገባቸው ሰዎች ለእራሳቸው እውቅና ከሰጡ፣ በይሉኝታ የሚሰማቸውን ህዝብ

ወዶና ፈቅዶ እንደሚያደምጣቸው አርገው እራሳቸውን ካሳመኑ ሰነባበቱ::

ጉድለቱን የማያስብ አገልጋይ ደግሞ በህይወቱ በጉ ለውጥ ሳለማምጣት እራሱን የዘጋ ምስኪን ነው::

መናገሩን እንጅ የማያደምጠውን አይቃኝም፣ ሰው ፊት መቆሙን እንጅ በዙሪያው ምን ያህል" የሰማይ ሰራዊት እንደተሰለፉ አይመለከትም ሲጮህ የሚጠላው ሁሉ ውስጡን ሲረብሸው የሰነበተውን እንጅ የክርስቶስን ወንጌል አይደለም::

አንተ ግን አገልጋይ ከሆንክ ሁል ጊዜም ትኩስ አገልጋይ ሁን እነ ቅዱስ ጴጥሮስን የነካው እሳት በእውነት ከነካህ አገልግሎት ሕይወት እንጅ ወረት እንዳልሆነ በእርግጥ ይገባሀል::

ዛሬ ዛሬ በእውቀት እንጂ በፀጋ የማያገለግል አገልጋይ መጥፋቱ ተረትና ምሳሌን እንጅ ወንጌል የሚገልጥ ደቀመዝሙር መታጣቱ ሞገስ በነበረው የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ላይ አሸዋ በተነበት እንጅ አላደገው አልተባለም:: ትናንትና በፍቅርና በእውነት ሲቀጣጠል የነበረው የአገልግሎት መንፈስ ዛሬ አሰመታየቱ የቀድሞ ትጋትና ብርታት ኀዘኑን ጠቅልሎ መንገዱ ያሰፈራል እንጅ አያበረታታም::

አሁን እንደፋሽን የተያዘውም የሚለቀጥጥ ጩኸት፣ እልባት የሌለው ንትርክ፣ የማይማርከውና ሕሲናን የማይገዛው ዝማሬ ሁሉ መጥፎ ነው ባይባልም ጥሩ ግን አይደለም::

እግዚአብሔር በፀጋ እንጅ በእውቀት አይገለገልም:: በኛ ውስጥ ያለው ጥቂት እውቀት ቤተ መቅደሱንና ህዝቡን ለመባረክ በቂ ሆኖ ከተገኘ ከእያንዳንዱ አገልጋይ የሚጠበቀው ቁም ነገር በእምነት





ለእግዚአብሔር መሰጠት ብቻ ነው:: ያን ጊዜ ባዶውን መሙላት የሚያውቅበት አምላክ ሁሉን እስከ ልኩ ይመላውና ወደ ተራራው ጫፍ ለአገልግሎት ያወጣዋል::

ለእግዚአብሔር መሰጠትና ቅዱሱን ህዝብ ማገልገል በብዙ አቅጣጫ ፈርጀ ብዙ በረከትና ጥቅም ቢኖረውም በዚህ ፀጋ ውስጥ ያሉ ሁሉ እንዴት ማገልገል እንደሚገባቸው ግን መዘንጋት የለባቸውም::

## ማን ማንን እንዴት ያገልግል?

የተጠራነው መዓድ ለማገልገል ሳይሆን ጌትነቱን ለማወጅ ነው:: ስለዚህ በሸለቆ ውስጥም ሆነ በሰገነት ላይ በድቅድቅ ጨለማም ሆነ በተገለጠው ብርሃን እርሱን ብቻ እናገለግለዋለን:: አገልግሎታችንም እንደዚሁ ይሆናል::

### 1ኛ. <u>ጸጋ ያለው ያገልግል</u>

ጸጋ የቃሉ ትርጉም ስጦታ ማለት ነው::

ሁሉም ሰው አይሰብክም፣ ሁሉም አይዘምርም ወይም ደግሞ ሁሉም አይቀድስም እያንዳንዱ ሰው ግን በጥምቀት ከመንፈስ ቅዱስ ሲወለድ ከተለያየ ፀጋ ጋር በእውነት ይወለዳል:: የፀጋው መጠን ደግሞ አንድም ሁለትም ዘጠኝም ሲሆን ይችላል እነዚህ ስጦታዎች እግዚአብሔርንና የእግዚአብሔርን ህዝብ በትህትና የምናገለግልባቸው መለኮታዊ በረከቶች እንጅ እንደ ኒሻን ደረታችን ላይ ለቅለን የምንኩራራባቸው ቁሳቁሶች አይደሉም::

❖ **ከጸጋው ጋር ያለ ሁሉ ባለማጉረምረም ያገልግል**

ጸጋን ማወቅ እራሱን የቻለ አንድ ጸጋ ስለሆነ የምናገለግልበትን ቦታ በጉልበት ከመቆጣጠራችን በፊት ጸጋዬ ነው ወይስ አይደለም ስንል ከእራሳችንና ከፀጋ ሁሉ ባለቤት ጋር በፀሎት እንነጋገር::

ጥቂት አገልጋዮች ያለ ፀጋቸው በማገልገላቸው ምክንያትና ቢያንስ የሚያምኗቸው ባልንጀሮቻቸውን አስተያየት ሳይቀበሉ በማገልገላቸው ስንቱ ነጠላ ተከናንቦ እንደሳቀና ስንቱ እንደተበሳጨ ያስተዋለው የአገልጋይና የተገልጋይ ህሊና ነው::

ልዑሉን ለማገልገል ከተቀበልናቸው ፀጋዎች መሀል የተኛውም ፀጋ ከየትኛው ፀጋ አይበልጥም ተቀምጦ ፀጋን ማማረጥ ከፀጋ ጫወታዎች ውጭ ያደርጋል::

ባለው ፀጋ ጌታውን የሚያገለግል አገልጋይ ግን እርሱ ልባም አገልጋይ ነው:: ምን ጊዜም እርሱ የሚሰራበት ፀጋ ጌታውን እንደሚያስደስተው ያምናል::

## 2ኛ. <u>መንፈስ ያለው ያገልግል</u>

አንድ አንድ ጊዜ መንፈስና ስሜት እንደ አብርሃምና ሎጥ በጉች እየተቀላቀሉ ያስቸግሩናል:: በመንፈስ ነን ስንል በስሜት ሆነን እንገኛለን ስሜት ነው ብለን ህሊናችንን ስናሳምነው ሁሉን የሰራው መንፈስ ሆኖ እናገኘዋለን:: ልባም አገልጋይ ግን ከስሜት ይልቅ በመንፈስ ቢያገለግል መልካም ይሆንለታል በመንፈስ የሚዘሩ አገልጋዮች ሁል ጊዜ ከመንፈስ ቅዱስ እርሻ ላይ በረከትን ያጭዳሉ ስሜት ግን ምን ጊዜም





ፍሬ የለውም:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን መንፈስ ወደ ምድረበዳ በወሰደው ጊዜ አሸነፈ እንጅ አልተሸነፈም ዛሬም አምላኩን የሚያገለግል አገልጋይ በመንፈስ ቢያገለግል ያሸንፋል::

## 3ኛ. <u>የተዘጋጀ ያገልግል</u>

ያለ ዝግጅት ለአገልግሎት መውጣት ያዋርዳል እንጅ አያስከብርም ያሳቅቃል እንጂ አያጸግንም:: አሁን አሁን የአገልግሎት መድረኮች ሁሉ የጨረባ ተዝካር ይመስል በጫጫታ የተሞሉት የዝግጅት ጊዜ ባጠራቸው አገልጋዮች ምክንያት ነው:: በአገልግሎት ታሪክ ውስጥ ያለ ዝግጅት የተሳካለት አገልጋይ የለም ሁሉም አገልጋይ የጾም፣ የፀሎት፣ የንባብ፣ የልምምድና የቅድስና ዝግጅት ያስፈልገዋል::

ታላቁ መምህር ኢየሱስ ክርስቶስ የዝግጅት ጊዜ ነበረው:: መጥምቁ ዮሐንስም ለእስራኤል እስከታየበት ቀን ድረስ በበረሃ ነበረ ይህ የዝግጅት ጊዜ ነው:: *ማቴ 4÷4 ሉቃ 1÷80*

እኛም ተዘጋጅተን በአቅማችን እናገልግል:: ያን ጊዜ በአገልግሎታችን ውጤታማ እንሆናለን::

# ክፍል - 6

## ግፈኞቹ

«ጌታም ተጠማሁ አለ:: ብዙ ያም ሆምጣጤ የሞላበት ዕቃ ተቀምጦ ነበር እነርሱም ሆምጣጤውን በሰፍነግ ሞልተው በሁሶፕም አድርገው ወደ አፉ አቀረቡለት ኢየሱስም ሆምጣጤውን ከተቀበለ በኋላ ተፈፀመ አለ፥ ራሱንም አዘንብሎ ነፍሱን ሰጠ::» ዮሐ 19፥29

ይህ ስለሁላችን በክርስቶስ ላይ ሆነ:: አይሁድ አንድ በሞትና በህይወት መካከል ቆሞ ውሃ ለሚለማመን ምስኪን ሰው በጭካኔ የዝሆን ሀሞት አጠጡት:: ከዚህም የበለጠ ግፍ ከዚህም የሚከፋ ርኩሰት የለም::

ትናንት ጌታን ሀሞት የጋቱት የግፈኞቹ ልጆች ዛሬ ግፉን ሁሉ ዘመናዊ አርገውት በገዛ ወገኖቻቸው ላይ የረቀቀ ብቀላ፣ የተጠና ግፍ መዋላቸው የደም ንክኪው ቢቀሰቅሳቸው ነው::

አሁንም በድሃው እንባ የሰበሰቡትን ጨርቅ የሚያለቀልቁ በሰው ከንፈር ጫማቸውን ሚያስጠርጉ፣ የህሊናቸው የጨለማ ጥልቀት መስኪያ ሜትር የሌለው የመስቀሉ ስር ግፈኞች ይገመቱ እንደሆን እንጅ ቆጥሮ የሚጨርሳቸው የለም::

ትናንት የእግዚአብሔርን ልጅ በእርጥብ እንጨት አንጠልጥለው በሰፍነግ ሀሞት በዘንጋቸውም ምሬት የጋቱትን ሰዎች ምናልባት ዛሬ መልካቸው ተቀይሮ ቢሆን ነው እንጅ ከመስቀሉ ስር አይታጡም:: ግፍን ግፈኞች ግፍ እንደሆነች አያውቋትም የግፍ





ወንበር፣ የግፍ ስልጣን፣ የግፍ ገንዘብ፣ የግፍ ብልፅግና ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት አፀያፊዎች ናቸው::

ለእራሳቸው የማር ወለላ እየላሱ አሽከሮቻቸውን በሻገቱ ስንዴ የሚያኖሩ፣ እነርሱ የተልባ እግር፣ ሱፍ ገበርዲን እየለበሱ ባሮቻቸውን በአቡጀዲ ሚገንዙ (የሌሊት ልብስ) እየሰቡ የሚያከሱ፣ እየኖሩ የሚቀብሩ እነዚህ ሁሉ ግፈኞች እንጅ የክርስትናው እሳት ያልነካቸው ደንዛዞች ናቸው::

ሁሉንም እግዚአብሔር ለፍርድ ይሰበስባቸዋል:: እርዮን ያልተማረ መሀይም ነው ብሎ ዳዊት በቀለምና በወረቀት ግፍ ቢውልበት የየዋሀን አምላክ እግዚአብሔር ግን ተበቀሎለታል::

አናብስቶቹ አክዓብና ኤልዛቤል የናቡቴን የወይን እርሻ ለመቀማት በግፍ ቢያስገድሉትና ሬሳውንም በውሻ ቢያስበሉትም እንኳ የደሀው ተሟጋች እግዚአብሔር በተመሳሳይ ሞት ቀጥቶለታል::

ጉልበተኛው ቃየን አቅመ ደካማው አቤልን በድንጋይ ወግሮ ቢገድለው እርሱም በስተመጨረሻ ላይ ድንጋይ ተንዶበት ሞቷል:: «ለእያንዳንዱ እንደየስራው መጠን እከፍለው ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር ነው» ይላል የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር:: ራዕ. ዮሐ 22፥12

ማንኛውም ሰው በእራሱ ላይ እንዲደረግ የማይፈቅደውን ነገር በሌላው ላይ ሲያደርግ ከተገኘ ግፈኛ ያሰኘዋል:: የተማረው ባልተማረው ላይ፣ ዘመናዊው በባላገሩ ላይ ባለስልጣኑ በተራው ህዝብ ላይ የሚውለው አስቀያሚ ተግባር ሁሉ ግፍ ነው::

ዛሬ ላይ ቀን ተመቸኝ ሜዳው አስጋለበኝ ብሎ ማንኛውም ሰው ግፍን በወንድሙ ላይ ቢፈፅም የነገው ቀን ለእርሱ እጅግ አስቀያሚ ነው።

ነገ ጉልበተኞች ይደክማሉ፣ ባለፀጎችም ይደኸያሉ፣ አለቆችና ስልጣናት ሁሉ ከወንበራቸው ይወገዳሉ፡ያን ጊዜ ሁሉ የእግዚአብሔር ብቻ ይሆናል ታዲያ በዚህ ቀን ግፈኞች/ምን እድል ፈንታ አላቸው? መኖሪያቸውስ ወዴት ይሆናል? በዚህ ዓለም ላይ ግፍን አብዝተው የሚፈፅሙት ሰዎች እግዚአብሔርን የማይፈሩና በህልውናውም ፈፅመው የማያምኑ ናቸው።

ፈሪሃ እግዚአብሔርን በልምምድ ያስቀሩ ሰዎችና በጥቂት እውቀታቸውም ምክንያት አምላካቸውን የከዱ ሁሉ ለግፍ ኃጢአት ተላልፈው የተሰጡ ናቸው።

ዛሬ እንደ ፈርኦን በግፍ ጡጫ የሚማቱ የእግዚአብሔርን ህዝብ ቀን ከሌሊት ሚያስጨንቁ ለፒራሚዶቻቸውና ለህንፃዎቻቸው ግንባታ ብቻ ሲሉ እየገደሉ የሚኖሩ እነርሱ በመኖቻቸው ጥቂት ናቸው። «የደም ሰዎችና ሸንጋዮች ዘመናቸው ግማሽ አይሞላም» ***መዝ 54÷23***

ግፍን የተለማመደ ሰው ግፍ ሲፈፅም ስራ እየሰራ እንደሆነ እንጅ እየበደለ እንደሆነ በፍፁም አይሰማውም ለአምላኩ እራሱን በቀደሰበት ሰሞን እንኳን ከግፍ እርሻ ለመራቅ አያስብም ከአምልኮ ስርዓት ሲመለስ፣ ወንጌል ተሰብኮ ሲገባ፣ ስጋና ደሙን ተቀብሎ ሲመለስ ሁሉ እርሱ በወገኖቹና በሰራተኞቹ፣ በልጆቹና በትዳር ጓደኛው ሳይቀር ግፍን ይፈፅማል።





ለዚህ ነው በመጽሐፍ እንዲህ ተብሎ የተፃፈው በፆማችሁ ቀን ፈቃዳችሁን ታደርጋላችሁ ሠራተኞቻችሁንም ሁሉ ታስጨንቃላችሁ። «እነሆ ለጥልና ለክርክር ትጾማላችሁ በግፍ ጡጫም ትማታላችሁ ድምጻችሁንም ወደ ላይ ታሰሙ ዘንድ ዛሬ እንደምትጾሙት አትጾሙም» ***ኢሳ 58÷4***

የየቤታችን ሳያንስ በየአብያተ ክርስቲያኑ የምንፈፅመው ሁሉ ግፍ ነው።

<u>ለምሳሌ</u>

- ❖ እድሜልካቸውን የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ሲማሩ ኖረው ዘመድ ስለሌላቸውና የሚሰጡትን እጅ መንሻ ስላጣ ብቻ ደጅ የምናስጠናቸው ሰዎች ጉዳይ ግፍ ነው።
- ❖ ዛሬ ላይ አቅምና ስልጣን አለን ብለን ብዙ ዘመን ተምረው ቤተ ክርስቲያንን እናገለግላታለን ያሉትን፣ እምነቱን ተስፋ ያደረጉትን የቅድስት ሥላሴን መንፈሳዊ ኮሌጅ ደቀመዛሙርትን አልተመቹንም ብለንና ከዓለማውያኑ ጋር አብረን ወግነን ማባረራችን፣ የተቀሩትንም ማጉላላትና ማሰቃየታችን ግፍ ነው።

## <u>**ቁማርተኞቹ**</u>

«ልብሱንም ተካፍለው ዕጣ ተጣጣሉበት» ሉቃ 23÷34

ክርስቶስ ኢየሱስ ከተሰቀለበት መስቀል ስር በቀሚሱ ላይ እጣ የሚጣጣሉ፣ ገበጣና ሰንጠረዥ እየተጫወቱ በስቃይ የሚስቁ፣ በሞቱም ሚዘብቱ በርካታ ቁማርተኞች ነበሩ።

ቁማርተኞቹ ሆድና ጡንቻ እንጅ ጭንቅላት የሚባል ነገር ፈፅሞ የላቸውም።

ሰይፋቸውን እንደጨበጡ፣ በኀበጣው ዳር እንደተንጫጩ ጀምበር ያዘቀዝቃል እንጅ ፀፀት ብሎ ነገር በእነርሱ ዘንድ የለም:: ሰባቱ የርህራሄ ቃላት፣ በሰማይና በምድር የተፈፀሙት ተአምራት ለጌታና ለክርስቲያኖች ይሁኑ እንጅ ለእነርሱ ምናቸውም አይደሉ:: በጌታ መስቀል ስር ግን አንድ ፎማይካድ እውነት አለ ካልን የምንሰጠው ምስክርነት ከመስቀሉ ስር ቁማርተኞቹ መኖራቸውን የሚያረጋግጥ ነው::

እጅግ ጻድቅ ለመሆን ካልሞከርን በቀር ትናንትና ዮናስን ከመርከቧ ላይ ለመጣል እጣ ሲጣጣሉ የነበሩትን ሰዎች ሁሉ ዛሬ ከመስቀሉ ስር በግልፅ እናያቸዋለን::

የተማማሉ ይመስል ሁሉም ይዋሻሉ፣ ሁሉም በሽንገላ ቃል ይነጋገራሉ እግዚአብሔርን የሚፈራ ለእውነትም የተሰጠ ሰው በመካከላቸው የለም:: ያለው እውነታ ይህ ብቻ ነው::

ከደቀመዛሙርቱ መካከል የአስቆሮቱ ይሁዳ ቁማርተኛ ነው ይባል ነበረ በእርግጥም ቁማርተኛ ነው::

ጌታውን አሳልፎ በ30 ብር ሲሸጠው በልቡ አንድ ነገር ያስብ ነበር «እኔ ከሊቃነ ካህናቱ 30 ብሩን ልቀበልና ጌታዬን ልስጣቸው እርሱ እንደለመደው በሚያስደንቅ ተአምራቱ ከእጃቸው ሲያመልጥ በሰጡኝ ገንዘብ እንደአሻኝ እሆንበታለሁ» ብሎ ነበር::

ዛሬም የእግዚአብሔርን ድንቅ ስራ እያስታከኩ፣ የቤተክርስቲያንን ተወዳጅነት ተገን እያደረጉ ለግል ኑሮአቸው የሚቆምሩ እጅግ በርካቶች ናቸው::





የጌታው ፍቅር ከነካው አማኝ፣ የፈጣሪዋም ውለታ ከተደረገላት መበለት ለዘወትር ሳንቲም የሚናፍቁ፣ ወንጌል ሲሰበክ እየተኙ ሳንቲም ሲባል የሚነቁ እነዚህ ቤተ ክርስቲያንን የማይጠቅሟት የክፍለ ዘመኑ ቁማርተኞች ናቸው::እስኪ ይህንን ነገር ግልፅ ለማድረግ ያህል በዙሪያችን ያሉትን ጥቂት የቁማር አይነቶች ለመመልከት እንሞክር::

## <u>ቁማር አንድ:</u>

## <u>HIV AIDS እና ቤተክርስቲያን</u>

- የዘመኑን በሽታ ለአመል እያነሳን በእውነትና በትጋት ሰርተን ስርነቀል ለውጥ ከማምጣት ይልቅ በHIV AIDS ስም ለሁለት ቀን ስብሰባ ሲያውም በማዛጋትና በማንኳረፍ ለተጠናቀቀው አሳዛኝ ትዕይንት 2 እና 3 ሺ ብር የውሎ አበል መቀራመታችን የለየለት ቁማር ነው::

በእርግጥ በዚህ አስከፊ በሽታ ዙሪያ ቤተ ክርስቲያን ሞራሏን አሰባስባ መንቀሳቀስ መጀመሯ ይበል ያሰኝ ይሆናል:: ይሁን እንጅ በእዚህ ጥራትና እውነታ በጉደለው ፀረ HIV AIDS ዘመቻ ላይ ምን ያህል ውጤታማ እንደምትሆን ለመገመት ያዳግታል::

ምክንያቱም እሁን ባለው የአልማጮች ጉዞ ቤተ ክርስቲያን ተጉዛ ብዙ መሔድ ይቅርና፣ ብዙም ማዝገም አትችልምና ነው::

ሳይለፉና ሳይደክሙ እንደ ያዕቆብ በወንድሞቻቸው ልብስ ለመባረክ የሚቀርቡ፣ የውሎ አበል ጡሩንባ ሲሰማ ከየሸለቆው የሚሰበሰቡ፣ በቤተ ክርስቲያን ሀብት ላይ የተበተኑ ጩኸኞች በተሰማሩበት መስክ ሁሉ ውጤት የለም:: የሚለፉትና የሚሯሯጡት በሙሉ

ለእምነቲቱ፣ ለቤተ ክርስቲያን ሳይሆን ለማይሞላው ፍላጐታቸው ብቻ ነው። «አትሳቱ እግዚአብሔር አይዘበትበትም» *ገላ 6፥7*

HIV AIDS የሆዳሞች መተዳደሪያና ኑሮን መለወጫ ስጦታ ሳይሆን በሽታ ነው።

## **ቁማር ሁለት፡**

## **ሹመት ሽልማትና የቅጥር ጣጣ**

መጽሐፍ ቅዱስ «በደለኛውን ስለጉቦ ጻድቅ ለሚያደርጉ፣ የፃድቁንም ጽድቅ ለሚያስወግዱበት ወዮላቸው» ይላል። ኢሳ 5፥23

በእርግጥ በተከበረው በአምላካችን ቤት ለእውነትና ለሃይማኖታቸው የቆሙ በርካታ አገልጋዮች ቢኖሩም ሹመትና ሽልማትን አስመልክቶ ጠንከር ያለ ቁማር የሚጫወቱ፣ ቤተ ክርስቲያንን በየስፍራው ያስነቀፉ ጥቂቶች እንዳሉ ግን ለመካድ አይሞከርም።

በተለይ ህዝብ ጠርቀም በሚልባት አዲስ አበባና ከባህር ማዶ ባሉት አብያተ ክርስቲያኖቻችን የሚፈፀመው ቁማር ቀላል አይባልም።

አሁን አንድ አገልጋይ የሚለካው በተማረው ትምህርትና ባለው የመንፈስ ቅዱስ ፀጋ መሆኑ ቀርቶ በብሔሩና በጐሳው ወይም ደግሞ በሚያቀርበው እጅ መንሻ ብቻ ሆኗል።

ጥቂት የገቢ ምንጭ ያገኛሉ በሚባሉት አብያተ ክርስቲያናት ቅጥረኛ ሆኖ ለማገልገል በእግዚአብሔርም ፊት ለመቆም ከቀባሪዎቹ አፍ ቀድሞ የሚወጣው ጥያቄ አምስቱ አዕማደ ምስጢርን እና በባቱ ስርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ታውቃለህ? የሚል ነው። ይህ ምን ማለት እንደሆነ የማይገባው ካለ በዚህ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለመቀጠር





የሚያስችልህን 5ሺ እና 7ሺ ብር ጉቦ አለህ? ማለት ነው። ይህ ታዲያ ቁማር ላለመሆኑ ምን ማረጋገጫ ይኖራል?

## **ቁማር ሶስት ፡ -**

## **በፀጋ ስጦታዎች ማጭበርበር**

«የፀጋም ስጦታ ልዩ ልዩ ነው መንፈስ ግን አንድ ነው። አገልግሎትም ልዩ ልዩ ነው ጌታም አንድ ነው - - - በሁሉ የሚያደርግ ግን እግዚአብሔር ነው» ይላል። *1ኛ ቆሮ 12፥4*

በእርግጥ የሚያጠምቁና የሚፈውሱ፣ የሚምሩና የሚያስተምሩ በርካታ የእግዚአብሔር ልጆች ዛሬም እንዳሉ ይታመናል ይሁን እንጅ ይህ እውነት ሳይገባቸው ከመንፈስ ቅዱስም ስጦታ ተካፋዮች ሳይሆኑ በጥምቀትና በፈውስ ሰበብ በቤቱ ውስጥ የሚቆምሩ ጥቂት አይደሉም።

እውነቱን መግለጥ ካስፈለገ በጾምና በፀሎት እንጅ በሱዳን አስማት በእግዚአብሔር ቤት ፈውስ የለም፣ በህንድም የጥንቆላ ጥበብ አምላካችን አይከብርም። እንዲህ እያደረጉ በልዩ ልዩ ስፍራ የሚቆምሩትን ሁሉ ተጠበቁ እንላቸዋለን።

አባቶች በስንት ሱባዔ ያገኙትን ጸጋ ወደ ጐን በመተው ከመሬት ተነስተው እንፈውስ እናድን የሚሉትን አያድኑምና ተዉ በሏቸው። ወገናችንም በገነፈለ የስሜትና የፈውስ ናፍቆት እየተቻኮለ ወደ ጥፋት መንገድ እንዳይሔድ የድርሻዬን አበረክታለሁ። አምላካችን ህዝባችንን ይጠብቅ። እሜን።

# ክፍል - 7

# የፍቅር እናት

«በኢየሱስ መስቀል አጠገብ እናቱና ሌሎች ሴቶች ቆመው ነበር ኢየሱስም እናቱን ይወደው የነበረውንም ደቀመዝሙር ከአጠገቡ ቆሞ ባየ ጊዜ እናቱን አንቺ ሴት እነሆ ልጅሽ አላት - - -» ***ዮሐ 19፥25***

<u>ማሳሰቢያ</u> በተለይ ይህንን ርዕስ ከህሊናዬና ከታላቁ እግዚአብሔር ጋር ሆኜ ሳዘጋጅ ውስጡ የታተመውን እውነት ለዓለም ከመግለጥ እንጂ ፍርሃትን ከመፍራት አልያም የስጋ ሰባሾችን ጭብጨባ ከመናፈቅ አንፃር ብቻ እንዳልሆነ ግልፅ ማድረግ እፈልጋለሁ።

በየትኛውም አቅጣጫ ሆኖ የኢየሱስ ክርስቶስን እናት ድንግል ማርያምን የሚመለከት ፍጥረት አንድ እውነት ይገባዋል እሳለሁ እርሱም የአምላክ እናት መሆኗ ነው። «የጌታዬ እናቱ ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል?»***ሉቃ 1፥43***

ዳግመኛም ከእግዚአብሔርና ከምስክሮቹ ጋር የሚተባበር ሁሉ ወደዚህ ወደተሻለው የዘመናት እውነት ይምጣ እላለሁ ምክንያቱም እግዚአብሔርን የሚወድ የእግዚአብሔር የሆነውን ሁሉ ይወዳል።

የእግዚአብሔር ከሆኑት መካከል ድንግል ማርያም እግዚአብሔርን አቅርበን ያየንባት መስታወታችን ናት። ጥቂት ሰዎች በምን ምክንያት በጌታ እናት ላይ የተዛባ መረጃ እንደሚጨብጡ ባላውቅም እኔን የገባኝ እውነት ግን እነእርሱም እንዲገባቸው





እፈልጋለሁ። «ነገር ግን የዘመኑ ፍፃሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከህግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ» ***ገላ 4፥4***

ልዑል አምላክ አንድ ልጁን ወደዚህ ዓለም ሲልከው የሞት መውጊያውን ሊያጥፍ፣ የሲኦል መዝጊያዎችን ሊሰብርና ፍፁም ነፃ ሊያወጣን እንደነበረ በብዙ ምሳሌ በብዙ ኃይለ ቃል ተተርኮልናል። እርሱም ምንም አምላክ ቢሆን እንኳን የማዳን ስራውን ሊሰራ የፈቀደው ስጋ ለብሶ በመሆኑ ለዚህ ደግሞ ፈቃደኛ የሆነ ሰው ይፈልግ ነበር። በሌላ አገላለፅ ዲሞክራቱ እግዚአብሔር ዓለምን በማዳን ተግባሩ ውስጥ አስተዋጽኦ የምታደርግ ቅድስት ድንግል አስፈለገው።

ለዚህ ቅዱስ ተግባር ደግሞ የፍቅር እናት ማርያም ብቁ ነበረች መልአኩ ወደ እርሷ በተላከ ጊዜ ባለማንገራገር «እነሆኝ የጌታ ባሪያው እንደቃልህ ይደረግልኝ» አለች። ***ሉቃ 1፥38***

ይህ መሰጠት ለኔ በመጀመሪያ የገባኝ ነገር ነበር። እግዚአብሔር ዓለምን በማዳን ስራው ውስጥ አስተዋጽኦ የነበራት ቅድስት ሴት። ከእግዚአብሔር ጋር ለሚተባበሩት ሁሉ ልዩ ፍቅር አለን።

❖ «<u>ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ</u>» ***ሉቃ 1፥28***

ይህን እውነት ማንም ሰው ሊጋፋውና ሊቋቋመው የማይቻለው ፍፁም እውነት ነው። በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ የተባለላቸው ስለ መልካም ስራቸውም የተመሰከረላቸው በርካታ ቅዱሳን እንስት ነበሩ። ከእነዚህ ሁሉ ግን የአዳኛችን ዙፋኑ የኢየሱስ ክርስቶስ እናት ድንግል ማርያም የተለየች ናት።

ከዚህ ጋር ሁሉም የሚገርመኝን አንድ እውነት ልንገራችሁ:: በተለይ ከዚህ ሃይማኖት ራቅ ብለው ያሉት ወንድሞች በአላቸው የአገልግሎት መድረክ ሁሉ በመጽሐፍ ያሉትን የበርካታ ሴቶችን ታሪክ ሲተርኩና ሲናገሩ የጌታቸውን እናት የድንግል ማርያምን ስም ለመጥራት ለምን እንደሚጨነቁ አይገባኝም:: እባካችሁ ወንድሞቻችን ከንጉሰ ነገስቱ እናት ጋር እልህ አትጋቡ እርሷ የእሸናፊው የእግዚአብሔር እናት ናት::

በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 26 ቁ. 7 ላይ አንዲት ሴት ጌታን ሽቱ ብትቀባው ሴቲቱ ያደረገችው ነገር ወንጌል በሚገለጥበት ስፍራ ሁሉ እንደሚሰበክ ተጽፎላታል:: እስተውለን ካየነው የዚችን ሴት ስራ ከጌታ እናት ክብር ጋር ስንመዝነው ልዩነቱ የሰማይና የምድር ያህል ነው:: እንግዲህ ከዚህ እውነት አንፃር በፍቅር እናት በድንግል ማርያም ብንኮራ ምን ኃጢአት አለው? ሃይማኖታዊ ስሜት በጐ ህሊና ያለው ክርስቲያን ሁሉ ለጌታው እናት ፍቅርና አክብሮት ይኖረዋል በዚህም የመስቀሉ ፍቅር ምን ያህል እውነታን እንዳበራለት ለዓለም ይናገራል::

ጥቂት ሰዎች የጌታን እናት እመቤቴ ለማለት ድፍረት ያጣሉ ስለተወደደው ጸሎቷም (ምልጃዋ) ስንነግራቸው መርዶ እንደተነገረው ሰው ይደናገጣሉ:: ይህ ለምን ሆነ? ብለን ጥያቄ ስናነሳ ችግሩ የሰዎቹ ሳይሆን የሰዎቻቸው ውስጣዊ ጉስቁልና እንደሆነ ለመታዘብ በቃን::

ከውሃና ከመንፈስ ተወልዶ ክርስቶስን ጌታዬ ያለ ሁሉ የጌታውን እናት እመቤቴ ብሎ ቢጠራ ይከብርበታል እንጅ የጉዳና ላይ ነውጥ ቀለቃሽ ብሎ ወንኒ የሚወረውረው የለም::





በሃይማኖት መሰልጠን በእምነት አካሄድም መራቀቅ እግዚአብሔር ያከበራቸውን ሰዎች እየተነሱ ማዋረድ ሳይሆን እራስን ለእንዲህ ዓይነቱ ክብር በወንጌል ማዘጋጀት ነው:: እውነት የገባው ለፍቅርና ለእምነት የተሰጠ የሃይማኖት ሰው የጌታው እናት ዘላለማዊት እመቤት መሆኗ ካልተገለፀለት ይህ ሰው የገባ አህያው ረግጣ ከግንብ ያጣበቀችው እብድ ነቢይ ነው::

ዓለማችን እስከዛሬ ድረስ የምታስታውሳቸው እነ ልዕልት ዲያናና እነ ክልዮፓትራ ሌሎችም ምድራውያን ሴቶች እመቤት ከተባሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ እናት ለድንግል ማርያም ይህ ክብር ቢያንስ እንጅ አይበዛባትም::

ይህ በእንዲህ እንዳለ ሁላችንም ያልደረሰንበት አንድ አስገራሚ እውነት አለ:: እኛ የህይወት ግዴታ ሆኖ በዘመን ታሪክ ውስጥ ማስታወሻ ለመተውና እውነትን ለመግለፅ እንዕፋለን፣ እንሟገታለን እንጂ አሁን የኢየሱስ ክርስቶስ እናት ታላቂቷ እመቤት ከሙሉ ክብሯ ጋር በልጇ ቀኝ ናት:: ውዳሴና አምልኮ በነጩ ዙፋን ላይ ለተቀመጠው ለተሰዋው በግ ይሁን:: አሜን::

ለልጆቻቸው ፍቅርን መመገብ ለተሳናቸው ለዚህ ዓለም ወላጆች የፍቅር እናት ማርያም ድንቅ ተምሳሌት ናት:: ከቤተልሔም እስከምድረ ግብፅ፣ ከቤት እስከ አይሁድ ምኩራብ ከሊቶስጥራ እስከ ቀራንዮ ጫፍ ከውድ ልጇ አልተለየችም ለዚያ ነበር በመከራው ሰዓት ከመስቀሉ ስር በሀዘን ያየናት:: የተወደደው ፀሎቷ ከሁላችን ጋር ይሁን:: አሜን::

# ክፍል - 8

## አነጋጋሪው ስም

«የአይሁድ ንጉስ የናዝሬቱ ኢየሱስ» *ዮሐ 19፥19*

ይህን ጽሕፈት ጲላጦስና ጲላጦሳውያን በኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ላይ ያኖሩት ሀላፊ አግዳሚው ሁሉ በጌታ ሞት እንዲሳለቅ፣ በህማሙም እንዲያሾፍ በማሰብ ነበር።

ዘመን ለሁለት የተከፈለበት፣ የዓለም ህዝብ እንቆቅልሽ የተፈታበት፣ ሞት የደነገጠበትና ከሰማይ በታች ለሰዎች ሁሉ የተሰጠ ታላቅ ስም ኢየሱስ የሚለው አስደናቂ ስም ነው።

ስዚህ ስም የማይገዛ በዚህም ስም የማይሸነፍ ልዩ የሆነ ወገን የለም። በላይ በሰማይ፣ በታች በጥልቁም፣ በዚህ ዓለም ያለውና ገና ያልተፈጠረው ፍጥረት ሁሉ እንደ ብዙ ውሃዎች ድምጽ እያስተጋባ ለዘለዓለም ኢየሱስ ይላል።

ኢየሱስ የሚለው ስም መድኃኒት ማለት ብቻ ሳይሆን በራሱ መድኃኒት እንደሆነ ለኔ ገብቶኛል። ይህንን እውነት ሊሰርቀኝ የሚችል ምድራዊም ሆነ ሰማያዊ ኃይል የለም።

በእርግጥ አይሁድ ኢየሱስ የሚለውን ስም ለማጥፋት እንደ አማራጭ የወሰዱት ኢየሱስን በመግደል ነበር። የማይሞትን አካል ለመግደል ማሰብ፣ የማይጠፋን ስም ለማጥፋት መጣር አብደት እንጅ ጥበብ የለውም። የስሙ ትርጉም ያልገባቸው በእውነት ላይ የሸፈቱ ሁሉ ይህንን ስም ይቃወማሉ። እግዚአብሔርንም አጥብቀው ይፈትኑታል። እግዚአብሔር ግን አንድ ነገር ብቻ ያምናል ዓለምን





እንዲሁ ስለወደደ አንድ ልጁን ከሚያስደንቅ ስም ጋር ወደዚህ ዓለም መላኩን። ይህ የእግዚአብሔር ፍቅር ያከናወነው የማይዘነጋ ውለታ ኢየሱስ በሚለው ስም ውስጥ ለዝንተ ዓለም ታትሟል።

ኢየሱስ የሚለው ታላቅ ስም ከሰው ልጆች ታሪክ ጋር ባይቀላቀል ኖሮ ዓለም እስከ አሁን ድረስ አልጫ አልጫ እንዳለች ትሰነበት ነበር።

አልጋቸውን ይዘው የሮጡ፣ ከመቃብር ስፍራም የወጡ እንደ አንበሳ የዘለሉ፣ ዓይኖቻቸውን በብርሃን የሞሉ ሁሉ ኢየሱስ የሚለውን ስም ሲሰሙ የእንባ ሲቃ ይተናነቃቸዋል።

- ❖ ነቢያቱ ሁሉ የናፈቁት፣ ሲቃነ መላዕክቱ ያወጁት፣ ደቀመዛሙርት የሞቱለት፣ ህዝብና አህዛብ የተዋሀዱበት ታላቅ ስም ኢየሱስ የሚለው ስም ነው።
- ❖ የገሀነም ደጆች የፈራረሱበት፣ ጠላት ዲያቢሎስ መራር ጩኸት የጮኸበት፣ ሞት የዛለበትና አለማመን የራቀበት ልዩ ስም ኢየሱስ የሚለው ታላቅ ስም ነው።
- ❖ የአዲስ ኪዳን ታሪክ የጣፈጠበት፣ የነፃነት ሰንደቅ ያውለበለብንበት፣ አባ አባት ብለን የተከላተፍንበት የፍቅር ስም ኢየሱስ የሚለው ልዩ ስም ነው።
- ❖ የገነትን ደጃፍ ያንኳኳንበት፣ የበፍታ ኤፉድ ለብሰን የዘመርንበት፣ ባህርና የብሱን የገዛንበት ታላቅ ስም አየሱስ የሚለው ነው።

«ጉልበት ሁሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይንበርከክ። ምላስም ለእግዚአብሔር ክብር ይገዛ» *ፊሊ 2፥10*

አይሁድ በአንድ ወቅት የጌታን ደቀመዛሙርት በዚህ ስም እንዳታስተምሩ ብለው በጽኑ አስጠንቅቀዋቸው ነበር:: ደቀመዛሙርቱ ግን የመለሱት መልስ «ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባል» የሚል ነው:: *የሐዋ/ስራ 5፥27 - 32*

በእርግጥም ስጋ ለባሾችን ከማስደሰት እግዚአብሔርን ማስደሰት በእጅጉ ይሻላል:: ምክንያቱም እግዚአብሔር የእውነትና የታመነ አምላክ በመሆኑ እንደ ስጋ ለባሾች በሽንገላ ስለማይደሰት ነው::

ብዙ ጊዜ ጠላት በብዙ ጉዳና በብዙ አቅጣጫ የተከበረውን ስም እንዳንጠራ ገሀነማዊ ጫናዎችን በልዩ ልዩ መልኩ ወደ ህይወታችን ያመጣል:: አንድ አንድ ጊዜ እያስፈራራ፣ በሌላ ግዜ ደግሞ እያሳሳለስ ጠርተን የማንጠግበውን ታላቅ ስም ከውስጣችን ሊያወጣው ይባዝናል:: ከዚህ የተነሳ በርካታ ክርስቲያኖች ትላንትና በድፍረትና በፍቅር ሲጠሩት የነበረውን አዳኝ ስም ዛሬ ላይ ጋብ አድርገውታል::

እውነት እውነቱን ካወራን ግን ያለዚህ ስም ክርስትና፣ ያለዚህም ስም ድል የለም:: ይህ ስም በየትኛውም ቋንቋ የማይለወጥና የከበረ ታላቅ ነው::

ታላቁ የቤተ ክርስቲያን ሰው አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ በሰዓታት ጸሎቱ «ሐመርነ ዘኢይቀርቦ ሞገድ መዝገብነ ዘኢይሰርቆሰራቂ ፃዔ ወቁንቁኔ ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ» ትርጉም ሞገድ የማይሰብረው መርከባችን ሌባ የማይሰርቀው፣ ብልና ነቀዝ የማያጠፋውና የማያበላሸው ሀብታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ብሎታል::





መሐፍ ቅዱስ ይህንን ስም ለሰዎች ሁሉ የተሰጠ ታላቅ ስም ይለዋል:: «እንድንበት ዘንድ ለሰዎች ሁሉ የተሰጠ ስም» የሐዋ.ሥራ 4፥12

በሕይወታችን ውስጥ የሚፈፀመው እያንዳንዱ የኑሮ ስኬት ከዚህ ስም ጋር የተያያዘ በመሆኑ ማንኛውም ሰው በፍቅርና በእውነት ሆኖ ይህንን ስም ቢጠራ ሊፈረድበት አይገባም::

ጥቂት ሰዎች ኢየሱስ የሚለው ስም ሲጠራ ለምን እንደሚበሳጩ አይገባኝም:: ግን የምር ሲከፉቸው አይቻለው:: እነዚህ ሰዎች የሚጠሉት ስሙን ይሁን ስሙን የሚጠራውን ሰው በእርግጠኛነት አላወቅኩም::

ይህንንም ስም ጮክ ብሎ ለሚጠራው ሁሉ የጥላቻና የጥርጣሬ መንፈስ ያድርባቸዋል:: ምስጋና ክብር ለስሙ ይሁን:: አሜን::

# ክፍል - 9

## «ይከብዳል»

## አጭርና ግልፅ መልዕክት ለቅዱስነትዎ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በዘመናት ታሪክ ውስጥ ከገጠሟት እሳዛኝና አስደንጋጭ ዘመናት መካከል ይህ የቅዱስነትዎ የአመፃ ዘመን ከሁሉ የተለየና ነገሮች ሁሉ አቅጣጫቸውን የሳቱበት ነው ስል ቅዱስነትዎን በመድፈሬ ሀፍረት ቢጤ እየተሰማኝ ነው::

በእርግጥም አንድ በራሱ የተከበርኩና የተወደድኩ ነኝ እያለ የሚያስብን ምስኪን ሰው ተሳስተሀልና ታረም ብሎ መናገሩ በእኛ ሀገር እንደ እብደት እንጅ እንደ ጤናማ አያስቆጥርም:: ከዚህ አንፃር በአንድ ሺ አንድ ጉዳይ ላይ ከኔ በቀር ማን አለ እያሉ ለሚያስቡት ለቅዱስነትዎ ይህንን ጦማር መላኩ በእውነት ከብዶ ታይቶኛል:: ይሁን እንጅ ቤተክርስቲያንን ከጥላቻ ለማትረፍና በዘመኑም አንድ የእውነት ታሪክን ትቶ ለማለፍ ግን እውነቱ ይሻፋል::

ቅዱስ አባታችን ሆይ አጠንብዎ የተሰበሰቡት ምስኪኖች ለእንጀራ ሲሉ ከሚያቀርቡልዎት የሽሙጥ ቅኔ በስተጀርባ ያለው እውነትና አሁን ህዝቡ በሙሉ የሚሰማው ስሜት ይህን ይመስላል - - - - - - - - - - -

አሁን በየትኛውም ስፍራ ያለ ኢትዮጵያዊ ይልቁንም እኔ የሃይማኖት አባቱ ነኝ ብለው በድፍረት የተናገሩለት ኦርቶዶክሳዊ ሁሉ





በቅዱስነትዎ ምክንያት እንገቱን ከደፋ እንደ እንቁ በሚያበራውም እምነቱ መሸማቀቅ ከጀመረ ብዙ ዘመን ሊሆነው ነው::

ዛሬ ዛሬ ከሚደሰትብዎና ከሚፅናናብዎ ወገን ይልቅ ምስልዎን ሲያይ የሚከፋው፣ ስምዎ ሲጠራ የሚያኮርፈው፣ ሲሰብኩስትም የሚያጉረመርመው ኢትዮጵያዊ ቁጥሩ እየጨመረ መጥቷል::

ትናንትና አባቶቹ የተጓዙበትን የመኪና ጉማ አጉንብሶ ሲስም የነበረው አማኝ ህዝብ ዛሬ ላይ በሃይማኖት መሪዎቹ ጀርባ ላይ መጮሁ ቢበደል እንጅ ባይገባውና ባያስተውል አይደለም::

ወትሮም የስማያት ጥበብ ሲገነፍል፣ ወንጌል ሲገሰጥ ሲበራ እውነትን የሚቀብር ህሊና፣ ሽንገላን የሚያስተናግድ አእምሮ በባትሪ ተፈልጉ አይገኝም::

በእርግጥ ከማይነጥፈው የቀለም ቀንዳችን ውስጥ እውነት ይቀዳ ከተባለ ቅዱስነትዎ የዶክትሬት ዲግሪዎን ያጠናቀቁ ጥሩ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተናጋሪ፣ የአሸበረቁ አማርኛችን አስወንጫፊ፣ ጥሩ ሰባኪና ሊልም ደህና ቀዳሽ መሆንዎን መመስከር ያስፈልጋል::

- ❖ በቅዱስነትዎ የፕትርክና ዘመን ከመንግስት ጋር ባለዎት የጠበቀ ወዳጅነት ሳቢያ ደርግ ወርሷቸው የነበሩትን በርካታ የቤተ ክርስቲያን ይዞታዎች አስመልሰዋል::
- ❖ ጥቂት ቢሆኑም መንፈሳዊ የትምህርት ተቋማትና ኮሌጆች ተከፍተዋል::
- ❖ በብዙ ሚሊዮን ብር መንበረ ፓትሪያሪክ በ4 ኪሎ አስገንብተዋል::
- ❖ በጥቂት የአዲስ አበባ ገዳማትና አድባራት አብያተ ክርስቲያናት ዙሪያ ጥቂት የልማት እንቅስቃሴዎች ታይተዋል:: ሁሉም

የሆነው ግን ትላንትና ፅንፈኞች በጥይት ደብድበው ከገደሉት ምስኪን ህዝብዎ መዳፍ በተሰበሰበው ድቃቂ ሳንቲም እንጂ እርስዎ ከአሜሪካ አስጭነው በአመጡት ዶላር አልነበረም::

ብፁዕ ወቅዱስ አባታችን ሆይ በዘመን ታሪክ ውስጥ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጥቂት መልካም ነገር እንዳደረጉላት ሁሉ ከትውልዱ ህሊናም የማይጠፋ በርካታ ስህተቶችን ትናንትናና ዛሬ በአምባገነንነት መፈፀምዎን እንኳን ተበዳዩ ህዝብ ልቦናዎም ያምነዋል::

በፕትርክና ዘመንዎ ሁሉ አልታዘዝዎ ባሉት አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ላይ እንደ ጦር ጄነራል ጦር ሲያዘምቱ፣ ቆመጥና ጥይት የያዙ ወታደሮችን ሲበትኑ ሰነበቱ እንጂ በሠላም ሲሸመግሉና የሚገባ የሃይማኖት አባት ስራን ሲሰሩ በፍፁም አልታዩም::

ለዚህ ደግሞ ባለፈው ሰሞን በአዲስ አበባ ቅድስት ልደታና በጉፋ ቅዱስ ገብርኤል አብያተ ክርስቲያናት የደረሰው ለቆቃ፣ በህዝቡና በካህናቱ ላይ የተፈፀመው የጭከና ተግባር ሁሉ ታሪክ የማይረሳው የጠቆረ ትዝታ ነው:: በእርግጥ እንዲህ አይነቱ አሳፋሪ ተግባር የአንድ ሀሳባዊና ምድራዊ ሰው እርምጃ እንጅ በጉቼን ጠብቅ፣ ግልገሎቼን አሰማራ ተብሎ ሰማያዊ አደራን ከተቀበለ መንፈሳዊ መሪ እንደማይጠበቅ ግልፅ ነበር:: ይሁን እንጅ የሆነው ሁሉ በቅዱስነትዎ ዘመን ሆኗልና ይከብዳል::

ከዚህ ውጭ አሁንም ህዝቡ ያጉረመርማል:: ፈር የለቀቀው የጉሰኝነት በሽታ፣ የማይፈወሰት የዘረኝነት ደዌ ገራገራውን እየዘለለ ወደ መቅደሱ የዘለቀው ከትላንትና ይልቅ በቅዱስነታቸው ዘመን ነው ይልዎታል:: በእርግጥም እኮ ክርስቶስ ግሪካዊና አይሁዳዊ፣ ልጅና





ባርያ የለም ክፍፍል ተወግዷል ብሎ በሰበከባት ቤተ ክርስቲያን ጉጠኝነት ተዘርቶባት ትግሬ ከአማራው፣ ጉራጌ ከኦሮሞው ተለያይቶባት መመልከቱ ያበሳጫል እንጅ ደስታን አይጭርም::

ቅዱስ አባታችን በአንድ ወቅት አንዱን ሊቀጳጳስ «አባ እገሌ» ብለው ጠርተው «ጉሳን ትቀድሳለህ እንዴ?» ሲሏቸው «እንዴታ? ከእርሶ እግር ስር ቁጭ ብዬ እንደቀፀልኳት ነዋ!» ብለው እንደመለሱለዎት አንድ ወዳጄ አጫውቶኛል:: እኔ ግን አልሰማሁም:: እውነት ከሆነ የመልሱ ፍቺ ዛሬ ነው የገባኝ:: ጉሳ! ይከብዳል:: ኦ አባ ጉሰኝነት ለጠባቦች፣ ዘርም ለበቆሎና ለስንዴ ነው:: ለኛ ለእግዚአብሔር ልጆች ግን የአንዱ የአዳም ትውልድ እንደሆንን ከተሰበክልን ይበቃናል:: ስለዚህ በጠቅላይ ቤተ ክህነት እና በአንድ እንድ ወሳኝ ቦታዎች ያለውን የዘረኝነት መንፈስ አፅንተው ይዋጉት:: ለዚህም ጉሳና ብሔር የማይለየው አምላካችን ቅዱስ እግዚአብሔር ይርዳዎ እላለሁ::

መጽሐፍ «የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን እንድትጠብቁ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጐ ለሾመበት ለመንጋውና ለእራሳችሁ ተጠንቀቁ» ይላል:: *የሐዋ. ስራ 20፥28*

ቅዱስ አባታችን ከትላንትና እስከዛሬ ታላላቅ ስህተቶችን ለምን ያህል ጊዜ ተሳሳቱ? ለምን ያህል ጊዜ የሚባርኩትን ህዝብ ክፉኛ አሳዘኑ? ወይስ እኔ አልሳሳትም ብለው ደምድመዋል? የማይሳሳት እግዚአብሔር ብቻ ነው::

እኔ በአንድ መጽሐፍ ላይ እንዲህ የሚል ቃል አንብቤአለሁ «ሰው ይሳሳታል ከስህተቱ የማይማርና ይቅርታን የማይጠይቅ ሰው ግን ነገም ስህተቱን ለመድገም የበደል ቀጠሮ የያዘ ምስኪን ነው» ይላል:: ዛሬ ላይ በቤተክርስቲያናችን የሚደረገውን እየተመለከትን

ሁሉን የሚሰራው መንፈስ ቅዱስ ነው ብሎ ማመኑ እጅግ ይከብዳል:: አሁን እየተፈፀመ ባለው የቤተክርስቲያን አባቶች ስህተት መንፈስ ቅዱስና ቤተክርስቲያን ተጠያቂ አይሆኑም:: ተጠያቂዎቹ በእየእለቱ የሚስቱት ግለሰቦች ናቸው:: አሁን እየሆነ ያለውን ትችትና ተቃውሞም ወደ ቅዱስ ሲኖዶስና ወደ ቤተክርስቲያን ማጠጋጋት በፍፁም አይቻልም:: ህዝቡ እየተቃወመ ያለው ቅዱስነትዎንና የመስቀሉን አደራ የዘነጉትን ጥቂት ግለሰቦች ብቻ ነው::

ይህንን ታዲያ አምኖ መቀበል ወይስ ማስተባበል?

ቅዱስ አባታችን በብዙ ነገር ሆድ የባሰው ህዝብዎ መስከረም 16 ቀን 1998 ዓ.ም. በመስቀል አደባባይ ያን ሁሉ የተቃውሞ ጩኸትና እሪታ በእርሶ ላይ ሲያሰማ በወቅቱ ምን ተሰማዎ?

ጥላቻ ወይስ ፍቅር? ወይንስ ወንበዴ ነው አሉ:: የማይመለስ ጎሊና ምክንያት ይደረድራል:: ህዝቡ ሁሉ ከዳር እስከዳር እያስተጋባ «ይሁዳ ይሁዳ» እያለ ይጮህ ነበር:: በእርግጥ የዚያን ቀን ለእራስዎ ምን አሉ?

እኔ የምለው ቅዱስ አባታችን የረባ አማካሪ የለዎትም ወይ ብዬ ብጠይቅዎ ምናልባት ድፍረት ይሆንብኝ ይሆን? ብቻ ይከብዳል::

አሁን አማኙ ህዝብ በትክክል ነፍሱ የተሀየፈቻቸው በርካታ ነገሮች እንዳሉ ይገባኛል:: ከእነዚህ መካከል ግን የሃይማኖት አባቶች ከፖለቲከኞች ጋር መጣበቅ የሁል ጊዜ ብስጭቱ ነው:: ለዚህ ነበር ያ በዘመን ታሪክ ውስጥ አንኳን ለሃይማኖት መሪዎቹ ለማንኛውም የሰው ዘር አክብሮት የነበረው ኢትዮጵያዊ «ይሁዳ - - - ይሁዳ» እያለ በጠራራ ፀሐይ ሲጮህ የነበረው::





እኔ ያንንቀን ሰዎች «የቤተ ክርስቲያን የውርደት ቀን» ሲሉት ሰምቻለሁ:: በእርግጥም እንዲያ ነበር:: አባት ከልጆቹ ፊት ሲሸሽ ሲኮበልል ልጆችም ደፍረው በአባታቸው ጆሮ ሲጮሁ ያ ቀን ለኔ የመጀመሪያ ነው::

ቅዱስ አባታችን በአንድ ወቅት ዮሐንስ ጳውሎስ ዳግማዊ /ጆን ፖል/ የሮማው ቤተክርስቲያን አባት ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ በቀብራቸው ላይ ለመገኘት ከኢትዮጵያ ወደ ሮም እንደሄዱ አስታውሳለሁ:: በእርግጥም ጆንፖል ዓለም ሁሉ ሊያዝንላቸው የሚገባ ታላቅ ሰው እንደሆኑም አልጠራጠርም:: እንዲያ በመሆኑም ነው ጆን ፖል ሲያርፉ ሙስሊሙና ክርስቲያኑ፣ ህፃንና አዋቂው፣ በአለም ያለው የሰው ዘር ሁሉ ከፋኛ ሀዘን የመታው:: ምክንያቱም ጆን ፖል በሮማ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን በመላው ዓለም ተወዳጅ ናቸውና ነው::

እኔ የማስታውሰው አንድ አስደናቂ ነገር ቢኖር ታላቋ አሜሪካ በ2002 መከረኛዋ ኢራቅን ስትወር «ወረራው የግፍ ነውና ይህንን ነገር እኔና ቤተ ክርስቲያኔ አጥብቀን እንቃወመዋለን» በማለት በግንባር ቀደምነት ከተቃወሙት ሰዎች መካከል አንዱ የሮማው ፖፕ ታላቁ ጆን ፖል ናቸው::

ቅዱስ አባታችን እርስዎስ ዛሬ ቀን ከፍቶ ጨካኞች ምስኪን ደሀ ህዝብዎን አደባባይ ላይ ሲረሽኑት፣ ኢትዮጵያውያን በኢትዮጵያውያን ላይ ያለመራራት ሲዘምቱ ቅዱስነትዎ መች ተቃወሙ?

ከዓመት በፊት ጃፓኖች ሱናሚ በሚሉት የጐርፍ መጥለቅለቅ ሁለት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ዓለማችን 260,000 ዜጐቿን ስታጣ

በእርስዎ ትዕዛዝ ሰሞቱት ሰዎች በቤተክርስቲያን ጸሎት እንደተደረገላቸው የምናስታውሰው የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። ዛሬ ግን ለገዛ ወገንዎ የጸሎትን ቸርነት መከልከልዎ መላውን ኢትዮጵያዊ ከልብ መጉዳቱ ብቻ ሳይሆን የሚሰሩት ስራ ሁሉ ለጽድቅና ለበረከት ሳይሆን ለታይታ መሆኑን ያመላከተ ጎጸብራቅ ነው።

ግድያውን ባይቃወሙ እንኳን ሰቆቃና ሀዘን የከበደውን ኢትዮጵያዊ እህት ወንድም፣ እናት፣ አባት የሞተበትን መከረኛ ህዝብ ለማፅናናት መቼ ብቅ አሉ?

መስቀልን እኮ ማክበር የሚቻለው እንደ ክርስቶስ ለህዝብ እየሞቱ እንጅ በሽቶ የሰከረ ነጫጭ ቀሚስ እያጠለቁ አይደለም። ለዚህ ነበር ያ ምስኪን ህዝብ የተቃወመዎ።

ቅዱስነትዎ ግን ይህንን ተቃውሞ «የቤተ ክርስቲያን መደፈር» ሲሉ መግለጫና ውግዘት ቢጤ ማምሻውኑ አስነበቡ። ነገሩ ሁሉ ቁማርና ጫወታን ይመስላል። ታዲያ አይከብድም? ይከብዳል።

አስመታደል ሆኖ እንጅ እንደ መልካም አባትማ በእግዚአብሔርና በህዝብ ፊት ይቅርታ መጠየቁ ነበር። ታሪክን የሚሰውጠው። ግን እንዴት ተደርጎ? ምድራዊ ትልቅነት ክፉ ነው።

በአንድ ወቅት ወደ ክፍለ ሀገር ለአገልግሎት ወጥቼ በነበረበት ሰዓት አንድ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ትምህርቱን ያጠናቀቀ ወጣት አገኘኝና በ1993 ዓ.ም. በነበረው መለስተኛ ግር ግር ከፖሊሶች ሸሽተው ቅድስተ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ገብተው ስለነበሩት ተማሪዎች አጫወተኝና እርሱ ከእነርሱ አንዱ እንደነበረ አስታወሰኝ። በወቅቱ ተማሪዎቹ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ የገቡት ግርግሩ ጠንከር ስላለ ብቻ





ሳይሆን በሀገሪቷ ላይ ከወደቀው አስጨናቂ ፍርሃት የተነሳ ህዝቡ ታውኮ ስለነበር በዚሁ ጉዳይ ለመፀለይና በዚያውም ከወታደሮች ድብደባና እስራት ለመትረፍ ነበር። ሁኔታዎች ግን እንዳሰቡት አልሆነም። እንጠለልባት ብለው ያሰቧት ቤተ ክርስቲያን የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን አልነበረችምና ልጆቿን አሳልፋ ለሞትና ለእስራት ሰጠች። በቅዱስነታቸው ትዕዛዝ ተማሪዎቹ ከግቢው እንዲወጡ፣ የመንግስትም ወታደሮች ቤተ ክርስቲያኒቷን እንዲቆጣጠሯት ተደረገ - - - ያን ጊዜ የቆሰለ ሁሉ እስከ ዛሬ ድረስ አልተፈወሰም። ያኔ የጨከነም አንጀት እስከ አሁን ድረስ ይቅር አላለም። ይልቁንም አብዛኞቹ ተማሪዎች የቅዱስነታቸውን ስህተት የቤተ ክርስቲያን ስህተት አድርገውት ከአደጉባት ቤተ ክርስቲያን ጋራ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተሰያዩ። የሚልና ከዚህም የሚከብዱ ብዙ ነገሮችን አጫወተኝ። ሳላዝን ግን አልቀረሁም።

ቅዱስ አባት እግዚአብሔር የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን በዚህ ዘመን ያስባት።

ቅዱስ አባታችን - እንግዲህ በዚህ በቁጥር አንድ ትንሽዬ መጽሐፌ የህዝብዎን ወቅታዊ ትኩሳትና ውስጤ የነገረኝን የማይታበል እውነት ከባህር በጭልፋ ያህል ጽፌልዎታለሁ። ሌላ ሌላውን ለጊዜው መጻፍ አልፈለግሁም። ጊዜ አኑሬለታለሁ።

ምናልባት ይህች ትንሽዬ ጦማር ደርሰዎት በተረጋጋ ልቦና በስክነ መንፈስ እንደ አባት ከተፀፀቱ እሰየው። አለበለዚያ ግን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ህዝብ የጠላቸው አምባገነኑ ፓትርያሪክ ተብለው መጻፍዎ ለሁል ጊዜም ያሳዝነኛል። እግዚአብሔር ይርዳዎ።

በመጨረሻም በሳቱት ጊዜያውያን ላይ ብዕሬን እንዳነሳሁት ሁሉ ለቀናችዋ ሃይማኖት ክብር በእውነትና በፍቅር የሚደክሙትን ሊቃነጳጳሳቱን፣ ካህናቱን፣ ሰባክያነ ወንጌሉንና አሁን በዝማሬአቸው ምድርን እየከደኑ ያሉትን ዘማርያኑን ሁሉ ሳላመሰግን አላልፍም።

በተረፈ ግን ማንም አንዳች ቢጠይቀኝ የእኔ መልስ

«ዘጸሐፍኩ ጸሐፍኩ ፡- የጻፍኩትን ጽፌያለሁ» የሚል ነው።

ዮሐ. 19፥22

ይቆየን።